# አዲስ ዘመን

አኗድ

እሁድ 83 ዓመት ቁጥር 167 የካቲት 17 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# የሚኒስትሮች ምክር ቤት

## በተለያዩ ደንቦችና ስምምነቶች ላይ ውሳኔዎችን አሳለፈ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የሚኒስትሮች ምክር ቤት 27ኛ መደበኛ ስብሰባው በተለያዩ ረቂቅ ደንቦችና ስምምነቶች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ።

ምክር ቤቱ ትናንት ባካሄደው 27ኛ መደበኛ ስብሰባው በተለያዩ ሀገራዊ ፋይዳ ባላቸው ረቂቅ ደንቦችና የድጋፍ ስምምነቶች ላይ በጥልቀት ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል። ከተወያየባቸው ጉዳዮች መካከልም የደን ልማት ፣ጥበቃና አጠቃቀም ረቂቅ ደንብ ፣ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ጋር የተፈረሙ ሦስት የፋይናንስ ድጋፍ ስምምነቶች እና ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩትን በልማት ድርጅትነት ለማቋቋም የወጣውን ደንብ ለማሻሻል ረቂቅ ደንብ እንደሚገኙበት ተጠቅሷል።

የደን ልማት ፣ጥበቃና አጠቃቀም ረቂቅ ደንብ ሀገራችን ያላትን የደን ሀብት በአግባቡ ለማልማት፣ ለመጠበቅ እና በዘላቂነት ለመጠቀም፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችል ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የቀረበ ሲሆን፤ ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ...ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

## በሲቢኢ ኑር ስድስት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ደንበኞችን አፍርቷል

### -የሲቢኢ ኑር አገልግሎት በአንድ ሺህ 939 ቅርንጫፎች እየተሰጠ ነው

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሲቢኢ ኑር ስድስት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ደንበኞችን ማፍራት መቻሉን አስታወቀ። በመላ ሀገሪቱ የሲቢኢ ኑር አገልግሎት በአንድ ሺህ 939 ቅርንጫፎች እየተሰጠ መሆኑን ተጠቁሟል።

ከጥቅምት 22 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች "ስኬታማ ምዕራፍ፤ ብሩህ ተስፋ" በሚል መሪ ቃል ሲከበር የቆየው የሲቢኢ ኑር 10ኛ ዓመት ክብረ-በዓል ትናንት የማጠቃለያ መርሀ ግብር ተካሂዷል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ በወቅቱ እንደገለጹት፤ በኢትጵያ የተሟላ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት በመስጠት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ግንባር ቀደም ነው።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተሟላ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት መስጠት ከጀመረ 10 ዓመት ማስቆጠሩን ገልጸው፤ በዚህም ልዩ ልዩ የሸሪአ ሕግን የተከተሉ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ...ወደ ገጽ 5 ዞሯል



# በሕገወጥ ወረራ ምክንያት

## የባቢሌ ዝሆኖች ህልውና ለአደጋ ተጋልጧል

ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- በባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ ሕገወጥ የሰዎች ወረራ እየተስፋፋ በመምጣቱ ዝሆኖች ለህልውና አደጋ መጋለጣቸውን የጣቢያው ኃላፊ ገለጹ።

የባቢሌ የዝሆን መጠለያ ኃላፊ አቶ ባንኪ ቡደማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በእንስሳት መጠለያዎች ላይ የሚደርሱት የሰው ሰራሽ ችግሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ነው።

በሀገሪቱ ከሚገኙ የእንስሳት መጠለያ የጥበቃ ቦታዎች ውስጥ በቀደምትነት የሚጠቀሰው ይህ የዝሆኖች መጠለያም የዚህ ችግር ተጋላጭ ሲሆን፤ ለዚህም ሕገወጥ የሰዎች ወረራ በስፋት የሚጠቀስ ነው ብለዋል።

አቶ ባንኪ እንደገለጹት፤ መጠለያው በአጠቃላይ 6 ሺህ 982

በሕገወጥ ወረራ...ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# በኢትዮጵያ

## የዲጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባት ምቹ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ነው

ገጽ5



















ዜና



አቶ ሀብታሙ ታዬ

## በሰባት ወራት የተሰበሰበው ደም የ250 ሺህ ሰዎች ሕይወትን ታድጓል

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ሰባት ወራት የተለገሰው ደም በአማካኝ የ250 ሺህ ሰዎችን ህይወት መታደግ እንደቻለ የኢትዮጵያ ደምና ህብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት አስታወቀ። በሰባት ወሩ 189 ሺህ 579 ዩኒት ደም መሰብሰቡ ተጠቁሟል።

የኢትዮጵያ ደምና ህብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016 በጀት ዓመት ሰባት ወራት በመላ ሀገሪቱ የተሰበሰበው ደም በአማካኝ 250 ሺህ ሰዎችን ሕይወት ታድጓል።

በበጀት ዓመቱ ሰባት ወራት 240 ሺህ ዩኒት ደም ለመሰብሰብ ታቅዶ፤ 189 ሺህ 579 ዩኒት ደም ተሰብስቧል።ይህ የተሰበሰብ ደምም በአማካኝ የ250 ሺህ ሰዎችን ሕይወት መታደግ እንደቻለ አስታውቀዋል።

አንድ ሰው 450 ሚሊ ሊትር ደም ሲለግስ የሶስት ሰዎችን ሕይወት መታደግ እንደሚችል በመረዳት ኅብረተሰቡ በበጎ ፈቃደኝነት ደም በመለገስ የማይተካውን የሰው ልጅ ሕይወት መታደግ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

አቶ ሀብታሙ እንዳሉት፤ በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች በነበረው የጸጥታ ችግር ደም ባንኮች በሚፈለገው ደረጃ ደም ማሰባሰብ ባለመቻላቸው የተያዘውን እቅድ ማሳካት አልተቻለም ብለዋል።

አፈጻጸሙ ከክልል ክልል የተለያየ መሆኑን የተናገሩት አቶ ሀብታሙ፤ በአዲስ አበባ ከተማ፣ በኦሮሚያና ሶማሌ ክልሎች የተሻለ አፈጻጸም መኖሩን አመልክተዋል።

ሲዳማ፣ ማእከላዊ ኢትዮጵያና ደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች ላይ በቂ በጀት ባለመመደቡ የደም ልገሳ አፈጻጸሙ መካከለኛ ሲሆን፤ በአንጻሩ ከዚህ በፊት በርካታ ደም ሲሰበስብ የነበረው አማራ ክልል ደም ባንክ ባጋጠመው የጸጥታ ችግር ዝቅተኛ አፈጻጸም አስመዝግቧል ብለዋል።

የደም ልገሳው በተጠናከረ ሁኔታ እንዲቀጥል ማዕከል ላይ እየተሠራ ያለው ሥራ አበረታች ቢሆንም፣ በሀገሪቱ ወጥ የሆነ አሠራር እንዲኖር እና ሁሉም ማህበረሰብ የደም ልገሳ ሥራውን ባህል አድርጎ መቀጠል እንዲችል በትኩረት እንደሚሠራ ገልጸዋል።

የደም ልገሳ ባህሉን ለማዳበር በትምህርት ቤቶች፣ በሃይማኖት ተቋማት፣ በደም ልገሳ ክበቦች እና ማህበራት ጋር የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት የግንዛቤ ማስጨበጫና የንቅናቄ ሥራዎች መሠራታቸውን አስታውቀዋል።

ትምህርት ቤቶች ሲዘጉ፣በአጿማትና በበዓላት ወቅት የደም እጥረት እንደሚያጋጥም ያለፉት ተሞክሮዎች ያሳያሉ ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ በመጪው ወራት የክርስትና ሃይማኖት ጾም ሲገባ የደም እጥረት እንዳያጋጥም ማህበረሰቡ በበጎ ፈቃድ እንዲለግሱ ከወዲሁ እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

ሰዎች መስፈርቱን በደንብ ካለማወቃቸው የተነሳ ደም ለመለገስ መፍራታቸው ተግዳሮት መሆኑን ገልጸው፤ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራውን ማሳደግ ይጠይቃል ብለዋል።

የደም ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱን በመረዳት ማህበረሰቡ በበጎ ፈቃድ ደም እንዲለግሱ ጥሪ አቅርበዋል።

# የአዲሱ ሕንፃ ኤጀንሲውን በአፍሪካ ካሉ ቤተ-መዛግብት ቀዳሚ ተጠቃሽ እንዲሆን ያደርገዋል

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- አዲሱ ዘመናዊ ሕንፃ ኤጀንሲውን (ወመዘክር) በአፍሪካ አሉ ከተባሉ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጽሐፍት አንዱ ተጠቃሽ እንዲሆን ያደርገዋል ሲል የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻሕፍት ኤጀንሲ በ700 ሚሊዮን ብር ያስገነባውን ባለ 17 ወለል ሕንፃ በትናንትናው ዕለት አስመርቋል።



በወቅቱ ንግግር ያደረጉት የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ቀጄላ መርዳሳ እንደገለጹት፤ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተጠሪ የሆነው የኢትዮጵያ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻሕፍት አገልግሎት ከተቋቋመበት ከ1936 ዓ.ም ጀምሮ የሀገሪቱን የመረጃ ሀብቶችን በአንድ ማዕከል ሥር በማሰባሰብ ለጥናትና ምርምር እንዲውሉ ሲሠራ ቆይቷል። ይህን ትልቅ ሀገራዊ ኃላፊነትም ይበልጥ በዘመኑና በተደራጀ መልኩ ለመጪው ትውልድ በማስተላለፍ ላይ ይገኛል ብለዋል።

ተቋሙ የዕውቀት አስተዳደርን በማጎልበት በመረጃ የበለጸገ ኅብረተሰብን በመፍጠር ኅብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያደርግ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ አዲሱ ሕንፃም ተቋሙን በቴክኖሎጂ በማዘመንና ለኅብረተሰቡ ተደራሽ በማድረግ በአፍሪካ አሉ ከሚባሉት ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጽሐፍት አንዱ እንዲሆን የሚያስችለው መሆኑን አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻሕፍት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ይኩኖአምላክ መዝገቡ በበኩላቸው፤ አዲሱ ሕንፃ 17 ወለሎች ያሉትና በመንግሥት ከ700 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጎበት የተገነባ ነው፡፡

ሕንፃው መዛግብትን ለማደራጀት ምቹ ተደርጎ የተሠራ በመሆኑ ኤጀንሲው ሥራውን ዘመናዊ በሆነ መልኩ አጠናክሮ እንዲቀጥል የሚያግዘው ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ሕንፃው የቤተ መዛግብትና የቤተመጻሕፍት አገልግሎት ከመስጠት በተጨማሪ የስዕል ኤግዚቢሽን ማሳያ፣ የስዕል ስቱዲዮ፣ የሕፃናት ቤተ መጻሕፍት፣ የሥልጠና ክፍሎች፣ የመሰብሰቢያ አዳራሾች ያሉት መሆኑን ጠቅሰው፤ ጥናት ለሚያከናውኑ ሰዎች የተሻለ አገልግሎት የሚሰጥበት መሆኑን አብራርተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት ኤጀንሲ በ1936 ዓ.ም በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን መንግሥት የተመሠረተ ሲሆን፤ ከአዲስ አበባ በተጨማሪም በተለያዩ ክልሎች እንዲሁም በማረሚያ ቤቶች አብያተ መጽሐፍትን እያቋቋመ ስልጠና እየሰጠ የሚገኝ ተቋም መሆኑን ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል።

በተጨማሪም ተቋሙ የተመሰረተበትን 80ኛ ዓመት ክብረ በዓሉን ያከበረ መሆኑን ገልጸው፤ በመርሀ ግብሩ ላይም ከፍተኛ የመንግሥት አመራሮች፣ አርቲስቶች ፣ የሃይማኖት አባቶች ፣ የሚድያ ባለሙያዎችና እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

# ነፃ ሕክምናው የባለሙያዎችን የሥራ ጫና ከማቃለል ባሻገር ታካሚውን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው

ልጅዓለም ፍቅሬ

አዲስ አበባ፡- ነጻ ሕክምና ለመስጠት ወደ ኢትዮጵያ የመጡ የፖላንድ የሕክምና ባለሙያዎች በሆስፒታሎች ያለው የሕክምና ባለሙያዎች የሥራ ጫና ከማቃለል ተጨማሪ ታካሚውን ተጠቃሚ የሚያደርጉ መሆናቸው ተገለጸ።



በኢትዮጵያ ዲያስፖራ ማህበር አስተባባሪነት ነጻ ሕክምና ለመስጠት ከፖላንድ ለመጡ 30 በጎ ፈቃደኛ የሕክምና ባለሙያዎች በቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ትናንት አቀባበል ተደርጎላቸዋል።

ባለሙያዎቹ ከዛሬ ጀምሮ ለሚቀጥሉት ሰባት ቀናት በአዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታልና በጦር ኃይሎች ሆስፒታል እንዲሁም አርባምንጭ ከተማ ላይ የነጻ ህክምና አገልግሎት ይሰጣሉ።ከሚሰጧቸው የሕክምና አይነቶች መካከልም የጭንቅላት ቀዶ ጥገና፣ የሰመመን ሕክምና፣ የማህጸንና ጽንስ ሕክምና እንደሚገኙበት በወቅቱ ተጠቅሷል።

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ማህበር ፕሬዚዳንት ወይዘሮ ቅድስት ልዑልሰገድ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ የሕክምና ባለሙያዎቹ የሕክምና ባለሙያዎችን ጫና የሚያቃልሉና ታካሚውን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ናቸው።

ነጻ ሕክምናው የታካሚዎችን ኢኮኖሚ ጫና ከማቃላል አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ያሉት ወይዘሮ ቅድስት፤ የሕክምና ባለሙያዎቹ በኢትዮጵያ ዲያስፖራ ማህበር አስተባባሪነት ነጻ ሕክምና እንዲሰጡ መደረጉንና ወደፊትም የማስተባበር ሥራዎች በሰፊው ለመስራት እቅድ ተይዞ እየተሠራበት ይገኛል ብለዋል።

የነጻ ሕክምና ሰጪ ቡድን አስተባባሪ ብዙአየሁ መንገሻ (ዶክተር) በበኩላቸው፤ ነጻ ሕክምናው ሀገር ውስጥ ከሚሰጠው ተጨማሪ አዳዲስ ሕክምና የያዘ ነው። በተጨማሪም ከመሳሪያዎችና ከባለሙያዎች እጥረት የሚከሰቱ ችግሮችን ማቃለል የሚችሉ ናቸው ብለዋል።

ዶክተር ብዙአየሁ ከ36 ዓመት በላይ ፖላንድ ሀገር በሕክምና ያገለገሉ ሲሆን፤ባለሙያዎቹ ከተለያዩ ሆስፒታል የመጡ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

አሁን ለሦስተኛ ጊዜ ነው ነጻ ሕክምናው የሚሰጠው ያሉት ዶክተር ብዙአየሁ፤ በኢትዮጵያ በነበረው የሰሜኑ ጦርነት ወቅት ብዙ ጉዳት ለደረሰባቸው የጸጥታ አካላት ሕክምና መስጠት እንደቻሉ አስታውሰዋል።

በሰባቱ ቀናት በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ብቻ ለ60 ሕሙማን አገልግሎት ለመስጠት እቅድ እንደ ተያዘ ዶክተር ብዙአየሁ ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ብዙአየሁ ገለጻ፤ በተቋማት በኩል የሚደረገው ትብብር የተጓተተና አሰልቺ መሆኑ የነጻ ሕክምናውን ለማስፋፋትና አገልግሎቱን ለማፋጠን ተግዳሮት ነው። ነጻ አገልግሎቱ ከኢኮኖሚ፣ ከሙያና ከጊዜ አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ የሚመለከታቸው ተቋማት ድጋፍና ትብብር እንዲያደርጉ ጠይቀዋል።

በጦር ኃይሎች ሆስፒታል የመከላከያ የሕክምና ድጋፍ ሰጪ ቢኒያም መርድ በበኩላቸው፤ የነጻ ሕክምናው በሆስፒታሉ ከፍተኛ ችግር እያቃለለ የሚገኝ ነው ብለዋል።

ባለሙያዎቹ ለሆስፒታሉ ሀገር ውስጥ የማይገኙ መድኃኒቶችና ቁሳቁሶች ድጋፍ ማድረጋቸውን ያስታወሱት ቢኒያም፤ እስካሁን በተሰጠው ነጻ ሕክምናም ከመቶ በላይ ለሚሆኑ የሠራዊቱ አባላት የዓይን ሕክምና መስጠታቸውን ተናግረዋል።

በተጨማሪም ሀገር ውስጥ የማይገኙ መድኃኒቶች እጥረት ሲያጋጥም ድጋፍ እንደሚያደርጉላቸውም ነው የተናገሩት።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሰላም፣ ልማትና የሕዝቦች አብሮነት- ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ዕድገት!

በሕዝቦች መካከል የሚኖር መልካም ግንኙነት ለሰላም፤ ጠንካራ የሥራ ባህል ደግሞ ለልማት ጉልህ አስተዋጽዖ አለው። እነዚህ በአብሮነት ሰላምን፣ በትብብር ልማትን የሚያመጣ የዜጎች መስተጋብር ደግሞ፣ ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገትና ብልጽግና የማይተካ ሚና አለው። ምክንያቱም፣ ልማት ከትጋት፤ ሰላምም ከፍቅርና መተሳሰብ ይወለዳሉና።

ዛሬም ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ይሄንኑ አብዝተው ይሻሉ። ኢትዮጵያ የልጆቿን አብሮነት ትሻለች። ከአብሮነታቸው ደግሞ በፍቅርና መተሳሰብ የሚገነባ ሰላምን፤ ከትብብርና በትጋት የሚሳለጥ ልማትን፤ እነዚህ አብሮነትና ትጋት የሚወልዷቸውን ሰላምና ልማት ለሁለንተናዊ የሕዝብም፣ የሀገርም ብልጽግና አቅም አድርጎ መጠቀምን ትናፍቃለች።

በዚህ ረገድ፣ አንድ ሀገርና ሕዝብ ትናንት አለው። ዛሬ ደግሞ በእጁ ነው፤ ነገም የተስፋ መንገዱ ነው። እነዚህን ትናንቶች፣ ዛሬውንና ነገውን አሰናስሎ በመልካም ገጻቸው ጥቅም እንዲሰጡ ከተደረገ ያማረ ውጤት አላቸው። ካልሆነ ግን በተቃራኒው የንትርክ፣ የግጭትና የመነጣጠል ዕጣ ፈንታን ይደቅናሉ።

እኛ ኢትዮጵያውያንም ትናንቶቻችን በመልካምም፣ መልካም ባልሆኑም ሁነቶች የተሞሉ ናቸው። እነዚህ ሁነቶች ታዲያ ለዛሬው ማንነታችንና ለነገው ጉዟችን አቅምም፣ ሸክምም ሊሆኑም የሚችሉ ናቸው። ለምሳሌ፣ ላለፉት ሦስትና አራት አስርት ዓመታት፣ የእነዚህን የታሪክ ሁነቶች ክፉ ገጾች ብቻ በማስተጋባት በሕዝቦች መካከል አለመተማመን እንዲፈጠር፤ ቂምና ቁርሾ ሥር እንዲሰድድ የሚያደርጉ አካሄዶች ነበሩ።

በዚህም ኢትዮጵያውያን በበዳይነትና በተበዳይነት ስሜት ውስጥ እንዲገቡ፤ ይሄ ስሜት ደግሞ ለቂምና በቀል እንዲያዘጋጃቸው፤ በሂደትም እርስ በእርስ ወደ ግጭትና መነጣጠል እንዲገቡ የሚያደርጉ በርካታ አካሄዶች ነበሩ። ችግሩ በታሰበው ልክ ባይሆንም፣ መጠራጠርና መገፋፋቱ፤ መጋጨትና ለበቀል መነሳሳቱ ግን አልፎ አልፎ ታይቷል።

ዛሬም ድረስ ያልተሻገርነው ብሔርን፣ ሃይማኖትና ሌላም ማንነትን ማዕከል ያደረጉ ግጭትና መገፋፋቶች የዚህ አብነቶች ናቸው። እነዚህ ክስተቶች ደግሞ ሕዝቦች በጠንካራ መተማመን ላይ የተመሠረተ አብሮነታቸው እንዲፈተን፤ በፍቅርና ወንድማማችነት ስሜት ለይቅርታ የተገዛ ልባቸው እንዲሻክር፤ ብሎም ለጋራ ሀገራቸውና አብሮነታቸው የሚበጅ ትብብር ፈጥረው ልማታቸው ላይ እንዳያተኩሩ፤ አቅማቸውንም ከልማት ይልቅ ለግጭትና ጦርነት እንዲያውሉ የሚያስገድዱ ሁነቶችና ሁኔታዎችም ተፈጥረዋል።

እነዚህ ደግሞ ኢትዮጵያውያን በኅብር ደምቀው የሚገለጡባቸው የአብሮነት አውዶቻቸው እንዲደበዝዙ የሚያደርጉ ብቻ ሳይሆኑ፤ ሰላም እንዲርቃቸው፣ ልማታቸው እንዲደናቀፍና የታሰበው ብልጽግና እውን እንዳይሆን ታስቦ በውስጥም በውጪም እኩያን የሚፈጸም ተግባር ነው። በመሆኑም ይሄን ሁኔታ መቀየር እና ኢትዮጵያውያን መተማመን ላይ የተመሠረተ አብሮነታቸው፤ በአብሮነት በጠነከረ ክንዳቸው እውን ለሚሆን ልማታቸው፤ በፍቅርና ይቅርታ ለሚጸናው ሰላማቸው እንዲተጉ፤ በዚህም ሁለንተናዊ ብልጽግናቸውን እውን እንዲያደርጉ በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ አተኩሮ መሥራት ይጠበቃል።

በዚህ ረገድ ከ2010ሩ ሀገራዊ ለውጥ ማግስት የተሠሩና እየተሠሩ ያሉ ተግባራት መልካም የሚባሉ ናቸው። ምክንያቱም ከለውጡ ማግስት አንስቶ መንግሥት በሕዝቦች መካከል መተማመን፣ በኅብር የደመቀ አብሮነት፣ ሰላምና ሁለንተናዊ ብልጽግና እውን እንዲሆን የሚያስችሉ አቅጣጫዎችን ነድፎ እየሠራ ይገኛል።

ለምሳሌ፣ ለዜጎች ጥያቄ ምላሽ የመስጠት አካሄዱ ለዓመታት ተነፍጎ የቆየውን ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ መልሷል። በዚህም አዳዲስ የክልል፣ የዞንና ወረዳዎች ጭምር አደረጃጀቶች ተፈጥረዋል። የማንነት ጥያቄዎችና የወሰን ይገባኛል ቅሬታዎችም በውይይትና በምክክር ታግዘው በሕግ አግባብ እልባት እንዲያገኙም እየተሠራ ነው።

ከግንዛቤ ክፍተትም ይሁን ከራስ ፍላጎት አንጻር ብቻ ታይተው የተፈጠሩ ግጭቶች፣ እየታዩ ያሉ አለመረጋጋቶችም በውይይት እንዲፈቱ ተደርጓል፤ እየተደረገም ይገኛል። ዜጎች ያለፈ ታሪክ የግጭት ምክንያት እንዳይሆኗቸው ለማድረግም ሁሉን አቀፍ ውይይት እንዲያደርጉና ችግሮችን በይቅርታ ተሻግረው ነጋቸውን አብረው እንዲራመዱ ለማድረግም ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን አቋቁሞ እየሠራ ይገኛል።

ከዚህ በተጓዳኝ እዚህም እዚያም የሚታዩ አለመረጋጋቶችና ማኅበራዊ ጉዳዮችን ማዕከል ያደረጉ ችግሮችን ለመፍታት፤ በየክልል ከተሞች የሕዝብ ውይይቶች ተካሂደዋል፤ እየተካሄዱም ይገኛል። ይሄ ደግሞ ሕዝቡ ምን ይፈልጋል፤ ምንስ ሊደረግለት ይገባል፤ በምን አግባብስ ኃላፊነቱን ሊወጣ ያስፈልጋል፤… የሚሉ አንኳር ነጥቦችን ለመለየት አስችሏል።

ከሰሞኑም ከአማራ እና ኦሮሚያ ክልል የተውጣጡ ዜጎች በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ውይይት ሲያደርጉ እየታየ ነው። በዚህ ረገድ የአማራ ክልል ተወካዮች እና የኦሮሚያ ክልል ተወካዮች ከሁሉም ዞኖች ተውጣጥተው መምከራቸው ይታወሳል። ይሄ ደግሞ መንግሥት በየደረጃው የሕዝቡን ጥያቄ አድምጦ ለመመለስ ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው። ጅምሩም ሕዝቦች ጥያቄዎቻቸው እንዲመለሱላቸው እና መጠራጠሮቻቸው እንዲጠሩላቸው የሚያደርግ ነው።

በዚህ መልኩ የሕዝቦችን ቅሬታ አድምጦ መፍታት ሲቻል ደግሞ፤ መተማመን የተሞላበት ትብብር ይፈጠራል። በመተማመን ውስጥ የሚፈጠር ትብብር ደግሞ በጋራ ሠርቶ መልማትን፤ በፍቅር ተሳስሮ ለሰላም መቆምን ያጎለብታል። በዚህ መልኩ የሕዝቦች በመተማመን አብሮ መቆም፤ አብሮ በመቆም ልማትና ሰላምን እውን ማድረግ ሲቻል፤ ሀገር እንደ ሀገር የታሰበውን ሁለንተናዊ ልማትና ብልጽግና እውን ማድረግ ይቻላል። በመሆኑም ለሀገር ሁለንተናዊ ብልጽግና እውን መሆን መሠረት ለሆኑን ሰላም፣ ልማትና የሕዝቦች አብሮነት ያለ እረፍት መሥራት ከሁሉም የሚጠበቅ ተግባር ሊሆን ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

ኢፕድ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ያልገባን የዓድዋ ትምህርት

**በቁምላቸው አበበ ይማም(ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

በዓድዋ ድል ላይ በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ ምሁራን የተደረጉ ጥናቶች ፣ ምርምሮች፣ ድርሳናት፣ የኪነ ጥበብ ሥራዎች፣ ተረኮች እና አካዳሚያዊ ሙግቶች፤ ዓድዋ ከኢትዮጵያውያን አልፎ የአፍሪካውያን ከፍ ሲልም የጥቁር ሕዝቦች ድል መሆኑን የሚተርኩ ናቸው። የዓድዋን ድል ከዚህ አንፃር ብቻ መመልከት የአሸናፊዎች ታሪክ ብቻ እንዳያደርገው እሰጋለሁ። ዳሩ ግን ታሪኩ የተሸናፊዎች፣ የቅኝ ገዥዎች፣ የተስፋፊዎች ፣ የወራሪዎች ፣ የነጮች ጭምር አድርገን ስናየው የዓድዋ ድል ከጥቁር ሕዝቦች ድል አልፎ የሰው ልጆች ታሪክ፣ ገድል ይሆናል።

ፀሐፍት የዓድዋ ዘመቻ ከወሰደው ጊዜና ከሚያካልለው የቦታ ስፋት እንዲሁም በድል ከመደምደሙ አንፃር ሲታይ የ19ኛው መ. ክ .ዘ ታላቁ ጦርነት እንደሆነ ያወሳሉ። ዓድዋን አንድ እርከን ከፍ በማድረጉ ላይ ከተግባባን፤ ይሄን የሰው ልጅ ታላቅ ታሪክ የነበሩትን መግፍኤዎች፣ መነሻዎች ፣ ውጤቶችን አክለን ትምህርቱን የዘመናዊ ኢትዮጵያ እርሾነቱንም ለጋዜጣው እንዲመጥን ቀንጨብ አድርገን እንመልከታለን።

የፈረንሳይ ቱኒዚያን የመያዝ፣ የናፒየር ዘመቻ፣ የቤልጅየሙ ንጉሥ ኮንጎን የመቆጣጠር፣ የአውሮፓውያን የተስፋፊነት ሕልም፣ የስዊዝ ካናል መገንባትን ተከትሎ የቀይ ባሕር ጂኦ ፖለቲካዊ ጠቀሜታ ከፍ ማለቱና በወቅቱ የነበረው የዘውድ ሽኩቻ ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመያዝ ለመቋመጧ በመግፍኤነት ከሚጠቀሱት ሰበቦች ዋነኞቹ ናቸው። በጊዜው የንጉሥ ምኒልክ ወደዙፋኑ መቃረብ ያስደሰተው የጣሊያን ወኪል ፔትሮ ኢንቶኔል ግንኙነቱን በፊርማ ለማረጋገጥ ሚያዝያ መገባደጃ ላይ በ1881 ዓ.ም ውጫሌ ላይ የሁለትዮሽ ስምምነት ለመፈራረም በቃ።

ስምምነቱ ስውር ደባ ያለው ቢሆንም ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳው የባሪያ ንግድን ለማስቀረትና ጣሊያን ከኢትዮጵያ ጋር ላሰበችው የንግድ ልውውጥ እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚያገለግል ነበር። ዳሩ ግን ውሎ ሳያድር የስምምነቱ አንቀፅ 17 ውዝግብ አስነሳ። በዚህ አንቀፅ የጣሊያንኛ ቅጅ መሠረት ኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነቷን የምታደርገው በጣሊያን በኩል እንደሆነ የሚያስገድድ መሆኑ በተዘዋዋሪ ሀገሪቱን በጣሊያን ሞግዚትነት የምትተዳደር ያደርጋታል። የአማርኛው ቅጅ ግን የውጭ ግንኙነት ማድረግ ትችላለች ይላል። በስምምነቱ አንቀፅ 19 ላይ የአማርኛና የጣሊያንኛ ቅጅዎች እኩል ተቀባይነት እንዳላቸው መደንገጉ አለመግባባቱን አካረረው።

በ1887 ዓ.ም በወርሐ መስከረም በገበያ ቀን ቅዳሜ አፄ ምኒልክ ታሪካዊውን የ “ወረ ኢሉን ” ክተት አዋጅ አስነገሩ። « …ሀገርንና ሃይማኖት የሚያጠፋ ጠላት ባሕር ተሻግሮ መጥቷል። እኔም የሀገሬ ሰው መድከሙን አይቼ ብታገሰውም፤ እያለፍ እንደ ፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር ፤ አሁን ግን በእግዚአብሔር እርዳታ ሀገሬን አሳልፌ አልሰጠውም። ያገሬ ሰው ጉልበት ያለህ ተከተለኝ፤ ጉልበት የሌለህ በጸሎትህ እርዳኝ፤ …» አዋጁን ተከትሎ በአፄ ምኒልክ አዝማችነት፣ ከመላው ሀገሪቱ በከተቱት መኳንንትና መሳፍንት ባለሟልነት ከ100ሺህ በላይ ወዶ ገብ የገበሬ ጦር እና 29ሺ ፈረሰኞች በኢትዮጵያዊ አንድነት፣ ጀግንነት፣ ቆራጥነት፣ አልበገር ባይነት ፤ ዳርድንበሩን፣ ሉዓላዊነቱን ሊያስከብር ቀፎው እንደተነካ ንብ ወደ ሰሜን ተመመ። ጄነራል ባራቲየሪም ሠራዊቱን ወደ መሀል ትግሬ እንዲንቀሳቀስ ትዕዛዝ ሰጠ።

> « …ሀገርንና ሃይማኖት የሚያጠፋ ጠላት ባሕር ተሻግሮ መጥቷል። እኔም የሀገሬ ሰው መድከሙን አይቼ ብታገሰውም፤ እያለፍ እንደ ፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር ፤ አሁን ግን በእግዚአብሔር እርዳታ ሀገሬን አሳልፌ አልሰጠውም። ያገሬ ሰው ጉልበት ያለህ ተከተለኝ፤ ጉልበት የሌለህ በጸሎትህ እርዳኝ፤ …»

አፄ ምኒልክ ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ፋሽስታዊውና ወራሪው የጣሊያን ጦር ከግዛታቸው ለቆ እንዲወጣ ቢጠይቁም፤ ጄኔራሉ አሻፈረኝ ከማለቱ ባሻገር በዕብሪት የማይሆን ቅድመ ሁኔታ ይደረድር ጀመር፤ የአፄው ጦር ትጥቅ እንዲፈታ፣ ራስ መንገሻ እንዲታሰሩ፣ መላውን ትግሬን እንዲያስረክብ እና የጣሊያንን የበላይነት እንዲቀበል ጠየቀ። በዚህም ጦርነቱ አይቀሬ መሆኑ እርግጥ ሆነ። ወራሪው ጣሊያን የመጀመሪያውን የሽንፈት ኩታውን በሁለት ሰዓት ውጊያ አምባላጌ ላይ ተከናነበ።

የአምባላጌው አኩሪ ድል ኢትዮጵያውያን በጣሊያን ላይ የተቀዳጁት የመጀመሪያው ታላቅ ፋና ወጊ ድል ቢሆንም ፤ ከወታደራዊ ስኬቱ በላይ ሥነ ልቦናዊና ፖለቲካዊ ፋይዳው ከፍተኛ ነበር። ኢትዮጵያውያን የአውሮፓን ጦር ድል መንሳት እንደሚችሉ ያረጋገጡበት፤ የአፄ ምኒልክን ጦር የውጊያ ሞራል ያነቃቃ ከመሆኑ ባሻገር በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭም የንጉሡን ክብር ፣ ተቀባይነት ከፍ አደረገ ። የአፄ ምኒልክ ጦር ግስጋሴውን ቀጥሎ መቀሌን ተቆጣጠረ። ይሄን ተከትሎ ስብሀትና ሀጎስ የተባሉ ለጣሊያን ያደሩ ባንዳዎች ከድተው ለንጉሡ መግባታቸው ለወራሪው አስደንጋጭ መርዶ ነበር።

የንጉሡ ጦር በወርሐ የካቲት እኩሌታ ለዓድዋ ጥቃት ዝግጁ ሆነ። የጣሊያንና የኢትዮጵያ ጦር ወዲና

ወደ ገጽ 12 ዞሯል


ተማሪ ቤተልሄም ቀማቸው


ተማሪ በረከት ጎሳዬ


ተማሪ ቢሊሴ ጌታቸው

# የዓድዋ ድል የአሁኑ ትውልድ የራሱን ታሪክ ሠርቶ እንዲያልፍ የነፃነት መሠረት አስቀምጦለታል

-ተማሪዎች

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ ፡- የዓድዋ ድል ለአሁኑ ትውልድ የራሱን ታሪክ ሰርቶ እንዲያልፍና ለሀገሩ ልማትና ዕድገት እንዲታትር የነጻነት መሰረት አስቀምጦለታል ሲሉ ተማሪዎች ገለጹ። በዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ12ኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው ቤተልሄም ቀማቸው ለኢፕድ እንደገለጸችው፤ ዓድዋ ለኢተዮጵያዊያን የሁልጊዜ ኩራት የሆነ ታላቅ ድል ነው፡፡ ድሉ ሀገራችን ሉዓላዊነቷን ያረጋገጠችበት እንዲሁም ያላትን አቅምና ተጸእኖ ፈጣሪነት ለዓለም ያሳየችበት ነው፡፡

ከዓድዋ ድል የምንማረው አንድ ሀገር ላይ አለመግባባት ቢኖርም እንኳን የውጭ ወራሪ በሚመጣበት ጊዜ አንድ ሆኖ እንዴት ጠላትን መመከት እንደሚቻል ነው ያለችው ተማሪ ቤተልሄም፤

ይህም የሚያሳየው ምንም የግል ጥያቄ ቢኖርብንም ለሀገር ቅድሚያ መስጠት እንዳለብን ነው ብላለች።ተማሪ ቤተልሄም በተለይ የአሁኑ ትውልድ ታሪኩን ከማወቅ ይልቅ ማህበራዊ ሚዲያ ላይ የሚሰማቸውን ውል የሌላቸው መረጃዎች ላይ ጊዜውን ያጠፋል ስትል ገልጻ፤ ይህም እንደ ሀገር እንዳናስብ ያደርገናል ብላለች ።የዓድዋ ድል ለዚህ ትውልድ የሰጠው ነጻነትን በመሆኑ እኛም የራሳችንን ታሪክ ሠርተን ማለፍ እንድችል መሰረት ሆኖናል። ይህም ከእኛ በኋላ ላለው ትውልድ ትምህርት ይሆነዋል ስትል ገልጻለች።በአዲስ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ የሆነው በረከት ጎሳዬ በበኩሉ፤ አባቶቻችን በጦርነት ጠላትን አሸንፈው ጀግንነታቸውን አሳይተውናል ፡፡ እኛ የዚህ ዘመን ትውልዶችም ጀግና ለመሆን የግድ ጦርነት ላይ መሳተፍ አያስፈልገንም፡፡ ባለንበት ብቁ ዜጋ ሆነን ሀገራችንን የሚያኮራ ሥራ መሥራት ይኖርብናል ብሏል።ሀገራችንን የሚያስጠራ ሥራ ለመሥራት የዓድዋ ድል የሰጠን ማንነትን ማውቅና ነጻነት የዚህ ትውልድ ላይ ትልቅ ሚና አለው ሲል ተናግሯል።የዓድዋ ድል የነጻነት አርማ ነው ያለችው ደግሞ ተማሪ ቢሊሴ ጌታቸው ስትሆን ድሉ ኢትዮጵያ የአሸናፊነት መንፈስ ስልነበራት የተገኘ ነው ብላለች፡፡ ይህ የአሸናፊነት ስሜትም አሁን ላለው ትውልድ መተላለፍ ችሏል ስትል ገልጻለች ።

ሀገራችን ላይ ያለውን አንድነት አሁን ላይ ዘመን አመጣሽ በሆኑ ቴክኖሎጂዎች እየተሸረሸረ መጥቷል ያለችው ተማሪ ቢሊሴ፤ ይህም የአሁኑን ትውልድ በእጅጉ እየፈተነው ይገኛል ትላለች ።ይህንንም ትውልዱ ተረድቶ ታሪኩን ወደ ኋላ ተመልሶ በመመርመር ሚዛናዊ እና ሀገር ወዳድ ዜና መሆን ብቻ ሳይሆን ለሀገሩ ዕድገትና ብልጽግና ጠንክሮ መሥራት አለበት ብላለች።

# በኢትዮጵያ የዲጂታል ኢኮኖሚን ስመገንባት ምቹ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ነው

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**


ይሹሩን ዓለማየሁ (ዶ/ር)

አዲስ አበባ፡- የዲጂታል ኢኮኖሚን በመገንባት የማህበረሰቡን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ መሆናቸው የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ገለጸ።

በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የአይሲቲ እና ዲጂታል ኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ይሹሩን ዓለማየሁ (ዶ/ር) የዲጂታል ኢትዮጵያ ሳምንትን አስመልክቶ ትናንት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንደተናገሩት፤ በአሁኑ ጊዜ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ዓለምን እየተቆጣጠረ ይገኛል። በኢትዮጵያም መንግሥት የዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም ኢኮኖሚውን ለማሳደግና የማህበረሰቡን ጥያቄ ለመመለስ የዲጂታል 2025 ስትራቴጂ ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል ብለዋል።

በርካታ የአፍሪካ ሀገራትም የዲጂታል ቴክኖሎጂ በመጠቀም አገልግሎታቸውን በቀላልና ማህበረሰቡን ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ተደራሽ እያደረጉ ናቸው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ኢትዮጵያም በዲጂታል 2025 ስትራቴጂ ከተቀመጡት አንኳር ጉዳዮች መካከል የዲጂታል መሠረተ ልማት በመዘርጋት፣ የኢንተርኔት ተደራሽነት ማስፋት፤ የዳታ ማእከላትን መገንባት እንደሚገኙበት ጠቅሰዋል፡፡

እንዲሁም ዲጂታል ቴክኖሎጂ ለመጠቀም የዲጂታል መታወቂያ ማዘጋጀትና የሳይበር ደህንነት የማስጠበቅ፣ የኢ- ኮሜርስና የመንግሥትን አገልግሎት ዲጂታል በሆነ መንገድ ተደራሽ ማድረግ እንዲሁም በዘርፉ አስቻይ ምህዳር ለመፍጠር በክህሎት በፋይናንስና በሕግ ማእቀፍ ረገድ ዝግጅት ማድረግ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

በእዚህ ረገድም እስካሁን በተከናወኑ በርካታ ተግባራት ጠንካራ ኢኮኖሚ ያላት የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ይገኛል ብለዋል።

የዲጂታል ሳምንት ዝግጅትም ለማህበረሰቡ የኢትዮጵያን የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ሥራዎች ለማስተዋወቅ፤ ብሎም ኅበረተሰቡ የዲጂታል ቴክኖ ሎጂዎችን እንዲጠቀሙ ግንዛቤን በመፍጠር የዲጂታል ኢኮኖሚ እድገትን ለማፋጠን የሚጠቅም መሆኑን ገልጸው፤ መንግሥት የዲጂታል ቴክኖሎጂን ለልማት እና ለዕድገት በማዋል የማህበረሰቡን የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ቀላልና ቀልጣፋ ለማድረግ እያከናወናቸው ስላሉ ዘርፈ-ብዙ እንቅስቃሴዎች የሚቀርቡበት መሆኑንም ጠቅሰዋል።

በተጨማሪ የኢትዮጵያን የዲጂታል ሽግግር ጉዞ ገፅታዎችን የሚያጎሉ የተለያዩ አሳታፊ ተግባራትና ትምህርታዊ ዝግጅቶች የሚካሄዱበት ሲሆን፤ ማህበረሰቡ በዚህ ረገድ የተሰሩ ሥራዎችን በመከታተል መጠቀም የሚጠበቅበት መሆኑን አመልክተዋል።

የመጀመሪያው የዲጂታል ኢትዮጵያ ሳምንት በሀገር አቀፍ ደረጃ “የጋራ ጥረታችን ለዲጂታል ኢትዮጵያችን" በሚል መሪ ቃል በሀገር አቀፍ ደረጃ ከየካቲት 18 እስከ 22 ቀን 2016 ዓ.ም በተለያዩ መርሀ ግብሮች የሚከበር ሲሆን፤ ከሁሉም ክልል የሚመለከታቸው አካላትና የፌዴራል ተቋማት የሚታደሙበት መሆኑ በመግለጫው ተገልጿል።

# የሚኒስትሮች ምክር ቤት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ጋር የተፈረሙ 3 የፋይናንስ ድጋፍ ስምምነቶች ላይ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን፤ ስምምነቶቹ ለዲጂታል መታወቂያ አካታችነትና አገልግሎት አሰጣጥ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል የ300 ሚሊዮን ዶላር፣ ለትምህርትና ስልጠና ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል የ200 ሚሊዮን ዶላር እንዲሁም ለንግድ ሎጅስቲክስ ማሻሻያ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል የ90 ሚሊዮን ዶላር ብድር የሚያስገኙ መሆናቸው ተጠቅሷል፡፡

ምክር ቤቱም ሁሉም ብድሮች ወለድ የማይታሰብባቸው፣ የ6 ዓመታት የችሮታ ጊዜ ያላቸው እና በ38 ዓመታት ተከፍለው የሚጠናቀቁ መሆናቸውን በማረጋገጥ ረቂቅ አዋጆቹ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ በሙሉ ድምጽ መወሰኑ ተጠቁሟል፡፡

ምክር ቤቱ ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩትን በልማት ድርጅትነት ለማቋቋም የወጣውን ደንብ ለማሻሻል የቀረበውን ረቂቅ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

በተጨማሪም የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት እና የፌዴራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ተቋማት ለሚሰጧቸው አገልግሎቶች የሚከፈሉ የአገልግሎት ክፍያዎችን ለመወሰን በቀረቡ ረቂቅ ደንቦች ላይ ምክር ቤቱ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው ከወጡበት ቀን ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውሉ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

ምክር ቤቱም በአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ረቂቅ ፖሊሲ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ከጸደቀበት የካቲት 16 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

በይነ መንግሥታት የልማት ባለሥልጣን (ኢጋድ) ማቋቋሚያ ማሻሻያ ስምምነትን ለማጽደቅ በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይም ተወያይቶ ይጸድቅ ዘንድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

በመጨረሻም ምክር ቤቱ የተወያየው የብሮሚን፣ የግራናይት ፣የድንጋይ ከሰል እና የደለል ወርቅ ማድናት ልማትን የተመለከቱ አራት ረቂቅ ስምምነቶች ለሀገር ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያበረክቱና የመንግሥትን የፖሊሲ አቅጣጫ የተከተሉ ስምምነቶች መሆናቸውን በማረጋገጥ የማእድን ሚኒስቴር ስምምነቶቹን እንዲፈራረም እና ወደ ሥራ እንዲገባ በሙሉ ድምጽ ይሁንታ ሰጥቷል፡፡

ምክር ቤቱ ከጣሊያን መንግሥት ጋር በተፈረሙ 2 ፋይናንስ ድጋፍ ስምምነቶች ላይም ከተወያየ በኋላ ረቂቅ አዋጆቹ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ በሙሉ ድምጽ መወሰኑን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት መረጃ ያመለክታል፡፡

# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የፋይናንስ ሥርዓት በመዘርጋት ስድስት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ደንበኞችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን አስታውቀዋል።

በአሁኑ ጊዜ የሲቢኢ ኑር የባንክ አገልግሎት በአንድ ሺህ 939 ቅርንጫፎች እየተሰጠ እንደሚገኘ ገልጸው፤ በ156ቱ ቅርንጫፎች ሙሉ በሙሉ የሲቢኢ ኑር አገልግሎት የሚሰጥባቸው መሆናቸውን አመልክተዋል።

የሲቢኢ ኑር ተቀማጭ ገንዘብ ከ107 ቢሊዮን ብር በላይ የተሻገረ ሲሆን፤ የብሔራዊ ባንክ ደንብ እና መመሪያዎችን ተከትሎ በአካታች የፋይናንስ ሥርዓት በርካታ ደንበኞችን ተጠቃሚ እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

የሲቢኢ ኑር 10ኛ ዓመት ክብረ በዓል በአዲስ አበባ፣ በአዳማ፣ በጂማ፣ በድሬዳዋ እና በሌሎች ከተሞች ተከብሯል ያሉት አቶ አቤ፤ ባንኩ ስለሚሰጠው አገልግሎት ግንዛቤ የማስጨበጥ፣ አዳዲስ ደንበኞችን የማፍራት፣ የደም ልገሳ መርሀ ግብር እና ሌሎች ተግባራት ተከናውነዋል ብለዋል።

የሲቢኢ ኑር 10ኛ ዓመት ክብረ-በዓልን በማስመልከት የባንኩን ቋሚ ሠራተኞች በማስተባበር 715 ሺህ ብር ተሰብስቦ ለኢትዮጵያ ሕፃናት የልብ ሕሙማን መርጃ ማዕከል ማስረከባቸውንም ጨምረው ገልጸዋል።

ባንኩ እአአ 2023 በሳውዲ አረቢያ ጂዳ ላይ በራቴል ኢስላሚክ ባንኪንግ ሽልማት የተበረከተለት መሆኑን አውስተው፤ ሽልማቱ የተበረከተለት ባለፉት ዓመታት በፋይናንስ አፈፃፀም የኢስላሚክ ባንኪንግ አገልግሎትን ሳይሸራረፍ ተግባራዊ በማድረጉ እና ለሸሪዓ መርሆች ተግባራዊ በማድረግ ባስመዘገበው የላቀ አፈፃፀም መሆኑ አስታውቀዋል።

የብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዢ አቶ ሰለሞን ደስታ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ባንክ ለሀገር እድገትና ብልጽግና ወሳኝ በመሆኑ ሁሉምን የኅብረተሰብ ክፍሎች ያካተተ አገልግሎት የሚሰጡ ባንኮችን ማስፋፋት ይገባል።

ባንኩ በዜጎች መካከል የሚታየውን የሀብት ክፍፍልና የገቢ አለመመጣጠን ችግርን ለመፍታት፣ አካታች የፋይናንስ ሥርዓት ለመዘርጋት፣ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ፣ ለሥራ እድል ፈጠራ እና ሌሎች ጠቀሜታዎችን የሚያስገኝ ነው ያሉት ምክትል ገዢው፤ የፋይናንስ ተቋማትን በማሳደግ አካታች አገልግሎት እንዲሰጡ ከማድረግ አንጻር መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሰራ አስታውቀዋል።

በአነስተኛ የሥራ ዘርፎች ለተሰማሩ ዜጎች፣ ለአርሶ አደሮች፣ ለአርብቶ አደሮች እና ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች በቀላሉ ተደረሽ ሊሆኑ የሚችሉ የፋይናንስ አገልግሎት ሥርዓቶችን መገንባት እንደሚገባም ተናግረዋል።

የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ከዓለም አቀፍ ገበያ ጋር ያለውን ትስስር ወደላቀ ደረጃ ለማሻገር መንግሥት ዘርፉን ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት ለማድረግ አቅጣጫ ማስቀመጡን አስታወሰው፤ ባንኮች በሚሰጡት አገልግሎት ተወዳዳሪ መሆን እንዲችሉ በአቅም ግንባታ፣ በሰው ኃይል፣ በቴክኖሎጂ እና በተደራሽነት ከወዲሁ ሊዘጋጁ እንደሚገባ አስገንዘበዋል።

ለባንኩ ሁለተናዊ ዕድገት የበኩላቸውን ድርሻ ላበረከቱ አጋር ተቋማትም ዕውቅና ተሰጥቷል።

# በሕገወጥ ወረራ ምክንያት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ካሬ ኪሎ ሜትር (kilometer square) ስፋት ቢኖረውም በአሁኑ ወቅት 75 በመቶ የሚሆነው ክፍል በሕገወጥ የሰዎች ወረራ ተይዞ ከእንስሳት መኖሪያነት ወደ ሰዎች መኖሪያነት እየተለወጠ ነው።

በመጠለያው መሀል ድረስ ሰዎች በመውረር እርሻ ማስፋፋት፣ መኖሪያ ቤትና የሃይማኖት ተቋማትን መገንባት እና ከግጦሽ ማስፋፋት ባለፈ ለዝሆን ጥርስ እና ለምግብነት በማሰብ በዝሆኖች እና ቆላ አጋዘን ላይ ሕገወጥ አደን እንደሚካሄድም አስታውቀዋል።

በዘንድሮ ዓመትም 6 ዝሆኖች እና የቆላ አጋዘኖች በሕገወጥ አደን መገደላቸውን አቶ ባንኪ ገልጸው፤ይህንን ለመከላከል በአካባቢው ከሚገኙ የጸጥታ አካላት ጋር እየተሠራ ነው ብለዋል።

ይህ በእንስሳት በመጠለያ ቦታው ላይ የሚደረግ ሕገወጥ ወረራ በእንስሳቱ ላይ ከሚያደርገው ጫና በተጨማሪ በዚህ ገፊ ምክንያት እንስሳቱ ወደ ውጪ እንዲወጡ እና በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ ጥቃት እንዲያደርሱ እያደረገ መሆኑንም ገልጸዋል።

በተለይም በሚኖሩበት አካባቢዎች በተፈጥሮ ያገኙት የነበረውን ምግብ እና ውሃ ፍለጋ ከመኖሪያቸው ወጥተው ወደ ህብረተሰቡ በመቀላቀል ሰዎችን መልሶ በማጥቃት ጉዳት እያደረሱ መሆኑንና በዚህ ዓመት ብቻም አስራ ሁለት ሰዎች በዝሆኖች መገደላቸውን ኃላፊው አስታውቀዋል።

መጠለያው በሶማሌ ክልል እና በኦሮሚያ ክልል መካከል ላይ መሆኑ ችግሩ እንዳይፈታ ትልቅ ማነቆ ሆኗል ያሉት ኃላፊው፤ ከሦስት ዓመታት በፊት በተቀመጠ አቅጣጫ 700 ቤቶችን የማፍረስ ሥራ ተጀምሮ የነበረ ቢሆንም ሙሉ ለሙሉ ማስወጣት አለመቻሉንና የወጡት መልሰው የሰፈሩበት ሁኔታ እንዳለ ገልጸዋል።

በመሆኑም ችግሩን በመፍታት መጠለያውን የጋራ ሀብት በማድረግ እንዲሁም የፌዴራል መንግሥት ትኩረት በመስጠት በቅንጅት በመሥራት የፓርኩን ህልውና መታደግ ይገባል ብለዋል።

የባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ 6 ሺህ 982 ካሬ ኪሎ ሜትር ቦታ የሚሸፍን ሲሆን፤ በውስጡ ከ30 በላይ አጥቢ እንስሳት እና ከ200 በላይ የአዕዋፍ ዝርያዎች እንደሚገኙበት መረጃዎች ያመለክታሉ።

# የሕይወት ገጽታ

## በጎ አሳቢው በጎ ሰው

**ስምስም መንግሥቱ**

በአሁኑ የይርጋለም ከተማ፤ በቀድሞ ገበሬ ቀበሌ ማኅበር በነበረው  መሲንቾ ነው ተወልደው ያደጉት። መሲንቾ ቀድሞ በደቡብ አሁን ደግሞ በሲዳማ ክልል ውስጥ ነው የምትገኘው።

የመሲንቾ ፍሬ የሆኑት አቶ አርጋው አየለ መሲንቾ፣ አፈር ፈጭተው ከአብሮአደጎቻቸው ጋር ቦርቀው፣ የቀለም ትምህርት ተምረው፣ የእርሻ ሥራንም ቀስመው፣ ቤተሰብ ማክበርና መውደድን ሥነምግባርና ሰብአዊነትን ተጎናጽፈው የሕይወታቸውን መሠረት የጣሉት በትውልድ ቀያቸው ነው።

አስተዳደጋቸውን፣ የልጅነት ጊዜያቸውን እንዲህ ነበር ያጫወቱን፤«በገጠር ሳሎን፣ መኝታ ቤት፣ ኩሺና፣ ሌላ ተጨማሪ ክፍል የለም። አባት፣ እናት፣ ልጆች፣ የቤት እንስሳውም በአንድ ቤት ውስጥ ነው የሚያድረው። እናታቸው ልጅ ሲወልዱ ላሞቹም እኩል የሚወልዱባቸው አጋጣሚዎች ነው የነበሩት። እናታቸውም ላሞቹም ምጥ ሲያፋፍማቸው አያታቸው ነበሩ የሚያዋልዷቸው።»

እናታቸው ስምንት ልጆች ነው የወለዱት። አቶ አርጋው አራተኛ ልጅ ናቸው። ከጊዜ በኋላ ግን አባታቸው ሌላ ሚስት አግብተው ልጆች በመውለዳቸው የልጆች ብዛት ወደ 14 ከፍ ብሏል። አባታቸው ሁለተኛ ሚስት ያገቡት ከአቶ አርጋው እናት ጋር ፀብ ስለነበራቸው አይደለም። የአካባቢው ማኅበረሰብ በልማድ የሚያደርገውና እንደባህልም የሚወስደው በመሆኑ ነው። አባታቸው ከሁለተኛ ሚስታቸው ጋር ሲሆኑ የአቶ አርጋው እናት ብቻቸውን መሆኑን መረጡ።

የቀድሞ ባለቤታቸውን ሚስት ግን በጥሩ ወዳጅነት ነው የሚቀርቧቸው። ልጆችም ከሁለተኛ ሚስት ከተገኙት ልጆች ጋር ጥሩ የሆነ ግንኙነት አላቸው። በተለይም አቶ አርጋው ለአባታቸው ሁለተኛ ሚስት ጥሩ ስሜት አላቸው። በልጅነታቸውም አብረው ኖረዋል።

አቶ አርጋው አባታቸው ጎበዝ ገበሬ ብቻ ሳይሆኑ፤ በሥነምግባራቸው ትላልቅ ከሚባሉ፣ በሥራም ከፍተኛ የኃላፊነት ደረጃ ላይ ከሚገኙ ሰዎች ጋርም በመዋል ሀገራዊም ሆነ በተለያየ ጉዳይ ላይ ጠቅላላ እውቀት ያላቸው ንቁ የሚባሉ እንደሆኑ ይገልጻሉ። ይህ ነው የሚባል የትምህርት ደረጃ ባይኖራቸውም በመጠኑ ተምረዋል። ከተማ ቀመስም ናቸው።

ከተለያዩ ሰዎች ጋር በአብዛኛው የሚገናኙት በመዝናኛዎች ሥፍራ በመሆኑ ገንዘብ ሲያስፈልጋቸው እህል ወይንም ሌሎች ንብረቶችን በመሸጥ በመሆኑ ስለ ገንዘብ ሲጠየቁ «ሰው ገዛሁበት» የሚል ነበር መልሳቸው። አብረዋቸው ከሚውሉ ሰዎች የሚያገኙአቸውን ጥቅሞች ለመግለጽ ነው ይህን ቃል የሚጠቀሙት።

አቶ አርጋው እንደሚሉት አባታቸው ከተለያዩ ሰዎች ጋር መዋላቸው የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ በር ከፍቶላቸዋል። አብዛኛው ገበሬ የልጁን ጉልበት ለመጠቀም ነው ቅድሚያ የሚሰጠው። የእርሳቸው አባት ግን እንዲማሩ ነበር የሚያበረታቷቸው። ልጆች በእርሻ ሥራ፣ ከብት በማገድና የሚታዘዙትን ሁሉ በመሥራት ቤተሰብ እያገዙ ነው የተማሩት።

በገጠር ምቾት የሚባል ነገር የለም። ምግብም ቤት ያፈራው ነው የሚቀርበው።አካባቢው በእንሰትም የሚታወቅ በመሆኑ ከእንሰት የሚዘጋጅ ቆጮ፤ አንዳንዴም የበቆሎ ቂጣ ዋና ምግባቸው ነው። ማባያው ወተት አብሮ ይቀርባል። የቆጮው ተረፈምርት ደግሞ ለመኝታ ያገለግላል። ፍራሽን የሚተካው ሳርም አሹቾ  ይባላል። ቅያሪ ልብስም አይታሰብም።

አቶ አርጋው አሁን ሁሉ ነገር ተሟልቶላቸው እንኳን  የገጠሩን ያህል ጣዕም ያለው ሆኖ እንዳላገኙት ይገልጻሉ። በገጠሩ የኤሌክትሪክ መብራት፤ በአጠቃላይ ዘመናዊ የሚባል ነገር የለም። ለጥናት ጊዜ ነው ኩራዝ የሚለኮሰው። አለበለዚያ ቤት ውስጥ በሚነደው እንጨት ብርሃን ነው የሚጠቀሙት። ማታ ከነደደው እንጨት ፍም በአመድ ተዳፍኖ አድሮ ነው ለጠዋት ቁርስ መሥሪያ ደግሞ እሳቱ  የሚነደው። ፍሙ እንዳይጠፋ እርግጠኛ መሆን በሚቻልበት ሁኔታ ነው የሚዳፈነው።

ክብሪት መጠቀም የተለመደ አይደለም። ቢጠፋ እንኳን እሳት ከጎረቤት ነው የሚዋሱት። ሁሉም ሰው ሥራ ሠርቶ፣ ያለውን በጋራ ተካፍሎ፣ ባለው ነገር ተደስቶ  ነው የሚኖረው።  ሁሉንም ነገር የሚያሸንፈው ቤተሰባዊ ፍቅሩ ነበር። አቶ አርጋውም በዚህ ጊዜ ያገኙትን ደስታ ነው ዛሬም በዓይነኅሊናቸው በማስታወስና ለማጣጣም የሚሞክሩት።

ልጆችን በማነጽ የወላጆች ሚና የጎላ ቢሆንም የአካባቢው ማኅበረሰብም ያለው አስተዋጽኦ ልጆችን የተሻለ የሚያደርግ እንደሆነ የሚናገሩት አቶ አርጋው፤ የእርሳቸውን እናትና አባት አስተዳደግ በልዩ ሁኔታ ይገልጹታል። እርሳቸው እንዳሉት አባታቸው ሲበዛ ቁጡና ኮስታራ ናቸው። ልጅ የሚያቀብጡ አይደሉም። ያጠፋ ይገረፋል። እርሳቸውም የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ሆነው ከጓደኞቻቸው ጋር ቁማር ሲጫወቱ አግኝተዋቸው ገርፈዋቸዋል። ከተገረፉ በኋላ ወደ ቁማር ጨዋታው አልተመለሱም።

አባታቸው ልጆች የሚያስፈልጋቸውን በማሟላት አይታሙም። የእናታቸው ግን ከአባታቸው ይለያል። በዱላና በቁጣ ሳይሆን፣ በፍቅር ነው ከጥፋታቸው የሚመልሷቸው። የእናታቸው ዘዴም ጥፋተኝነት እንዳይኖር የሚያደርግ ሆኖ ነው ያገኙት።

አቶ አርጋው አባታቸው «ሰው ገዛሁበት» ብለው የሚሰጡት ምላሽ አሁን ላይ ነው የገባቸው። ሰው ለማግኘት የተለያየ ነገር እንደሚደረግ ከአባታቸው መማራቸውን ያስታውሳሉ።

ከአባታቸው ትልቅ ትምህርት ያገኙበትን አጋጣሚም እንዲህ ያስታውሳሉ።  ለአባታቸው የተለያዩ ነገሮችን ማድረግ በመቻላቸው በአባታቸው ዘንድ የተለየ ቦታ እንደሚሰጣቸው ያስባሉ። ታዲያ አባታቸውን ከልጆቻቸው ማንን አብልጠው እንደሚወዱ ይጠይቋቸዋል። የአባታቸው ምላሽ ከጠበቁት ውጪ ነበር የሆነባቸው።

ምንም ለማድረግ አቅም የሌለው በቤተሰቡ ድጋፍ የሚኖረው ልጃቸውም ሆነ ሌሎቹም ልጆቻቸው  ለእርሳቸው ልዩነት እንዳልነበራቸው ነበር በወቅቱ ምላሽ የሰጧቸው። አቶ አርጋውም በምላሹ ልባቸው ነበር የተነካው። አባታቸውን እንደፈጣሪ ተምሳሌት ነው ያዩዋቸው። አለማዳላትና በእኩል ማየትን ነው ከአባታቸው የተማሩት።

አቶ አርጋው፤ መልካም ዜጋ ሆነው እንዲያድጉ ቤተሰብ ብቻ ሳይሆን የአካባቢ ማኅበረሰብም ሚና እንደነበረው በማስታወስ፤ ለዛሬ ማንነታቸው ጥሩ መሠረት እንደሆናቸውና ባለውለታቸው እንደሆኑም ይገልጻሉ። በማኅበረሰቡ ውስጥ ያዩትን በጎ ሥራ እርሳቸውም በዚህ ውስጥ እንዲያልፉ እንዳደረጋቸውም ይናገራሉ። ሕይወት በትግል ውስጥ የሚታለፍበት እንጂ በምኞት የሚገኝ እንዳልሆነም ተገንዝበዋል።

እርሳቸውም ዛሬ የልጆች አባት በመሆናቸው፤ ከወላጆቻቸውም ሆነ ከማኅበረሰቡ ያገኙትን የቤተሰብ መምራት ተሞክሮ እንደጠቀማቸው ይናገራሉ። መሻሻል አለበት ብለው ያሰቡትን ግን በልጆቻቸው ላይ እየተገበሩት ነው። የእርሳቸው አባት ለልጆች የሚያስፈልጋቸውን ነገር የሚያሟሉ ቢሆኑም ለልጆቻቸው ፍቅር የሚያሳዩበት መንገድ ባለመኖሩ እንደሚወዷቸው እርግጠኛ አልነበሩም።

በተለይም ልጆች ወደ ጉርምስና ሲሸጋገሩ ስለሚገጥማቸው መጥፎም ሆነ መልካም ነገር ከአባታቸው ጋር የመወያየት ዕድሉ አልነበራቸውም። እንዲህ ያለው ነገር በዚያን ጊዜ እንደነውር ስለሚታይ ሊሆን ይችላል። ይሄኛውን መንገድ ነው እርሳቸው ለማሻሻል ጥረት ያደረጉት።

ምንም እንኳን እርሳቸው በተወለዱበት ጊዜ ያለው ነባራዊ ሁኔታና አሁን ዘመኑ የሚጠይቀው የልጅ አስተዳደግ የሚለያይ እንደሆነ የሚገነዘቡ ቢሆንም፤ በወላጆችና ልጆች መካከል ግልጽነት መኖር እንዳለበት ያምናሉ። በተለይም ጾታዊ ግንኙነትን በተመለከተና ስለ ዓለም ነባራዊ ሁኔታ ከልጆቻቸው ጋር በግልጽ የመወያየት ባህል በማዳበራቸውና እንደጓደኛም በመቅረብ ስለልጆቻቸው ፍላጎትና ያላቸውንም አስተሳሰብ ለመረዳት ችለዋል።

እርሳቸው ያለፉበትን መንገድም ለልጆቻቸው ብቻ ሳይሆን፤ ለልጆቻቸው እናትም ቢሆን ግልጽ ሆነው ነው ወደ ትዳር የገቡት። ሰው እራሱን መደበቅ የለበትም የሚል እምነት አላቸው። ከየትኛው ማኅበረሰብ እንደመጡና በምን ሁኔታ እንዳደጉ ለባለቤታቸው በእጮኝነት ዘመናቸው ነበር የነገሯቸው። ምስጢር ሆኖ የሚቆይ ነገር ዘግይቶ ችግር እንደሚያመጣና ትዳርንም እስከ ማፍረስ የሚደርስ ነገር እንደሚገጥም በሌሎች ላይ ደርሶ አይተዋል።

ስለትምህርት፣ የሥራ ሁኔታ፣ ወደ ትዳር የገቡበትን አጋጣሚና ስለቤተሰባቸው አቶ አርጋው እንዳጫወቱን፤ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ክፍል ድረስ ተወልደው ባደጉበት መሲንቾ ገጠር ነው የተማሩት። ወደ አራተኛ ክፍል ሲዘዋወሩ ይርጋለም ውስጥ በሚገኝ ሚሲዮን ትምህርትቤት ገቡ። በሚሲዮን እስከ ስምንተኛ ክፍል ከተማሩ በኋላ ደግሞ ይርጋለም ከተማ በሚገኝ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት እስከ 12ኛ ክፍል ተምረው ትምህርታቸውን አጠናቀቁ።

ፈጣንና ነገሮችን ቶሎ የሚረዱ፣ ጎበዝ ከሚባሉ ተማሪዎች መካከል እንደሆኑ እራሳቸውን ይገልጻሉ። አጋጣሚ ግን በ12ኛ ብሔራዊ መልቀቂያ ፈተና ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚያስገባ ውጤት አልመጣላቸውም። ውጤቱ ያልመጣላቸው ጎበዝ ተማሪ ስላልሆኑ እንዳልሆነ ነው የሚያምኑት። ውጤት ያልመጣላቸው ብዙ ተማሪዎች እንደነበሩም ያስታውሳሉ። በወቅቱ ግን ይርጋለም ሆስፒታል ውስጥ እየሠሩ መማር የሚችሉበትን ዕድል አግኝተው በሆስፒታሉ ውስጥ ረዳት የላቦራቶሪ ቴክኒሻን ሆነው ተቀጠሩ።

በሥራቸውም በትምህርታቸውም ውጤታማ መሆን የቻሉት በአጭር ጊዜ ነበር። በሆስፒታሉም ትጉህና ጎበዝ ሠራተኛ ለመባል ጊዜ አልወሰደባቸውም።




አቶ አርጋው አየለ

> **የሰላም ባንኩ ሀገር አሁን ከምትገኝበት ችግር እንድትወጣ የሚያስችል የእርቅ፣ የፍቅር፣ የአንድነት ሃሳብ ሁሉም ዜጋ እንዲያዋጣ ዕድል የሚያመቻች ነው**

የሥራ ዕድላቸውንም በማስፋት ገቢያቸውንም ለማሳደግ እንዲሁ ፈጣን ነበሩ። በሌሎች የሕክምና ተቋማት ውስጥ በመሥራት ከመደበኛ ደመወዛቸው ተጨማሪ ገቢ በማግኘት ኑሯቸውን ለመለወጥ ይጥሩ ነበር። ገቢያቸው አንድ ሐኪም በወር ደመወዝ ከሚከፈለው በላይ የሚሆን ነበር። የላቦራቶሪ ቴክኒሻን ባለሙያ ቁጥር ውስን በመሆኑም በቀላሉ ነበር በሌሎች ዘንድ እውቅና ያገኙት።

ውሎአቸውም ከእርሳቸው ዕድሜ በላይ ከሆኑ እና በትምህርትም ከሚበልጧቸው ሰዎች ጋር ነበር። በሙያው ከሚቀርቧቸው በሕክምና ውስጥ ካሉት ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ኢንጂነሮች፣ የሕግ እና ሌላ ሙያ ካላቸው ጋር ጭምር ነበር። በዚህም ከዕድሜ እኩዮቻቸው ጋር ተለዩ። ለመቀራረብ ቢሞክሩ እንኳን መግባባት አልቻሉም።

በዚህ ሁኔታ ለስድስት አመታት የላቦራቶሪ ቴክኒሻን ሆነው ሠሩ። በሆስፒታሉ የተመቻቸላቸውንም የትምህርት ዕድል አጠናቅቀው የምስክር ወረቀት  አግኝተዋል። በሕክምናው ውስጥ ለመሥራት ፍላጎቱ ስለነበራቸው የ12ኛ ክፍል ነጥባቸውን ለማሻሻል ዳግመኛ ፈተና በመውሰድ ጥሩ ውጤት በማምጣታቸው በነርሲንግ ሙያም ለመሥራት ትምህርት ጀምረው ነበር። ግን አልገፉበትም።

የሥራቸው፣ የትምህርታቸውና አብረዋቸው የሚውሏቸው ሰዎች ሁኔታ «እኔ ማነኝ» የሚለው ነገር በውስጣቸው እንዲፈጠር አደረገ። በትምህርታቸውም ሆነ በሥራቸው፣ አብረዋቸው ከሚውሉት ሰዎች ጋር የሚመጣጠን ሆኖ ባለማግኘታቸው ነበር ይህ ስሜት የተፈጠረባቸው። ከዚህ ሁኔታ ለመሸሽ የመጨረሻ ውሳኔያቸው የነበረው ከሀገር መውጣት ነው። ይህን ለማመቻቸት ደግሞ ዩክሬን ውስጥ የሚኖር የሚያውቁት ወዳጅ ስለነበራቸው እርሱ እንዲያመቻችላቸው አደረጉ። ዕድል ቀንቷቸው በትምህርት ዕድል እኤአ በ2000 ነበር ከኢትዮጵያ የወጡት።

ዩክሬንን ወደ እንግሊዝ ሀገር መሸጋገሪያ ለማድረግ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## በጎ አሳቢው...

ከ6ኛ ገጽ የዞረ

ነበር እቅዳቸው። በዩክሬን ውስጥ እየተማሩ ለስድስት ወር ያህል ነበር የቆዩት። በዚህ በአጭር ጊዜ ቆይታቸው አንድ የታዘቡት ነገር ደግሞ ዩክሬኖች ለጥቁር ያላቸው አመለካከት በጣም መጥፎ መሆኑን ነው። በትራንስፖርት ውስጥ እንኳን ጥቁር ካዩ እስከ መደብደብ የሚደርሱበት ሁኔታ ለመታዘብ ችለዋል።

ዩክሬን ኮሚኒስት በነበረችበት ዘመን ብዛት ያላቸው ጥቁሮች የነበሩበትና በኑሮም ጥሩ ደረጃ ላይ እንደነበሩ በታሪክ ተረድተዋል። ዩክሬናውያን ነፃ ሲወጡ ጥቁሮች የኢኮኖሚ አቅም መፍጠራቸው የቅናት መንፈስ እንዲያድርባቸው ስላደረጋቸው ወደ ጥላቻ እንደተቀየረም እንዲሁ ሰምተዋል። በዚህም በዩክሬን መቆየቱን አልወደዱትም።

ከዩክሬን በሕገወጥ መንገድ ለመውጣት ያደረጉት ሙከራም ለአንድ ወር ያህል አንገላቶአቸዋል። ሕገወጥ አዘዋዋሪዎቹ አንዳንዴ ከአሳማ ጋር ሌላ ጊዜ ደግሞ ለመቆየት ምቹ ባልሆነ ውስጥ ያሳድሯቸው ስለነበር ፈተናው ከባድ ነበር። ድንበር ለመሻገር ያጋጠማቸውን ፈተና ሁሉ ተቋቁመው በመጨረሻ ተሳክቶላቸው ወደ ሀንጋሪ ተሻገሩ።

በሀንጋሪም የስደተኞች መጠለያ (ካምፕ) ውስጥ ነበር የገቡት። በካምፑ ውስጥም ወደ ተለያዩ ሀገራት ለመሄድ የተዘጋጁ ወደ 28 የሚሆኑ ኢትዮጵያውያንን አገኙ። በካምፑ በነበራቸው ቆይታ የሚሲዮን አስተማሪዎች ወደ እነርሱ በመምጣት የሥነልቦና ምክርና የኃይማኖት ትምህርት (መጽሐፍቅዱስ) ያስተምሯቸው ነበር።

አቶ አርጋው፤ በኃይማኖታዊ ትምህርቱ ተስበው ስደተኛ መሆናቸውን እስኪዘነጉ ነበር በዚያው መቆየቱን የመረጡት። አብረዋቸው የነበሩት ሁሉ በየተራ ሲሄዱ እርሳቸው አላስተዋሉም። አንድ አመት አለፋቸው። በኋላ ላይ ከካምፕ ወጥተው ወደ ከተማ ሄዱ። ሥራም ጀመሩ። እየሠሩ ለመማር መኖሪያ ፈቃድ ማግኘት ስላለባቸው ተንቀሳቀሱ። ተሳክቶላቸው ያሰቡትን አሳኩ። በባይብል ኮሌጅ ውስጥ ነፃ የትምህርት ዕድል አግኝተው፤ ለሦስት አመታት የኃይማኖት ትምህርት ተምረው በመጀመሪያ ዲግሪ ተመረቁ።

ትምህርት ከጨረሱ በኋላ ጊዜያቸውን በአግባቡ ለመጠቀምና ለቁምነገር ለማዋል እንዳለባቸው ለራሳቸው ቃል ገቡ። ይህን ቃላቸውን የሚያፀናላቸው የግራኅናቸውን አገኙ። እርሳቸው በተማሩበት ኮሌጅ ከአሜሪካን ሀገር የመጣች ወጣት ጋር ተዋወቁ። ከወጣቷ ጋር ተዋውቀው ሃሳብ ሲለዋወጡ የተጎዳን ማገዝ፣ መርዳት የእርሷም ፍላጎት ነበር። በተለይ ደግሞ እንዲህ ያለውን በጎ ተግባር ኢትዮጵያ ውስጥ መሥራት እንደምትፈልግ በነገረቻቸው ጊዜ የበለጠ ተቀራረቡ።

ወጣቷ ስለኢትዮጵያ የምታውቀው ነገር ኖሯት አይደለም። ኢትዮጵያም የት እንደምትገኝ አታውቅም። ግን በአንድ ወቅት በኢትዮጵያ ተከስቶ በነበረ ድርቅ ብዙ ሰዎች መጎዳታቸውን በመስማቷ ነበር እንዲህ ያለው ሃሳብ ወደ አእምሮዋ የመጣው። ሰዎችን በሥነልቦና፣ በሕክምና በሌላም በምትችለው መርዳት ዘማሪ መሆን ፍላጎቶቿ ነበሩ። ዓላማቸው አንድ ሆነ፤ ትውውቁ ወደፍቅር ተቀየረ። ብዙም ሳይቆዩ ወደ ትዳር ገቡ። እኤአ 2005 ነበር ጋብቻቸውን የፈጸሙት። አቶ አርጋው ያኔ 22 አመታቸው ነበር።

አቶ አርጋው ከሚኖሩበት ሀገር የመኖሪያ ፈቃድም አግኝተው ስለነበር ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ጊዜ አልወሰዱም። ከባለቤታቸው በፊት ከሌሎች በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጋር ሆነው ወደ ኢትዮጵያ መጡ። እንደመጡም አዲስ አበባ ከተማ የክብር ዶክተር አበበች ጎበናን የሕፃናት ማሳደጊያ ጎበኙ። የብዙዎች እናት የሆኑትን የክብር ዶክተር አበበች ጎበናን በጎ ተግባር ካዩ በኋላ በዕድሜ ዘመናቸው በትምህርትና በሥራ ልምድ ያገኙት ተሞክሮ ተደምሮ እርሳቸው የሠሩትን ያህል ሆኖ እንዳላገኙት ነው በወቅቱ የተሰማቸው። በመቀጠል ሀዋሳም ሄደው ነበር።

ከሀገር ቤት መልስ ከባለቤታቸው ጋር በውጭ ሀገር አልቆዩም። ጋብቻቸውን በአሜሪካን ሀገር ካደረጉ በኋላ ነው ወደ ኢትዮጵያ የመጡት። እኤአ 2006 (ጥር 1997 ዓ.ም)። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ሀዋሳ ውስጥ እየኖሩ ነው። አቶ አርጋው ባለቤታቸውን ይዘው ወደ ሀገር ሲመጡ ፈተናው ከቤተሰባቸው ነበር የጀመረው።

ባዶ እጃቸውን መምጣታቸው ብቻ አልነበረም የውጭ ዜጋ አግብተው መምጣታቸው ጭምር ነበር ያስወቀሳቸው። ቤተሰብ እነርሱንም ወደ ውጭ ያወጣል ብለው ሲጠብቁ እንዳሰቡት ባለመሆኑ ነበር ቁጣቸው የበረታው። የኃይማኖት ተቋማት ጭምር ነበር ከውጭ ሀገር መመለሳቸውን ያልደገፉላቸው። ሃሳባቸውን የሚረዳላቸው ሰው ለማግኘት ጊዜ ወስዶባቸዋል።

ይሄ ሁሉ ግን ጥንካሬን እንጂ ከዓላማቸው ወደ ኋላ እንዲሉ የሚያደርጋቸው አልነበረም። ባልና ሚስቱ መኖሪያቸውን ካመቻቹ በኋላ እየተጋገዙ ያሰቡት በጎ ሥራ ውስጥ ገቡ። ወደ ሥራው ሲገቡም ባንክ ውስጥ ገንዘብ አስቀምጠው ሳይሆን ልባቸው ውስጥ ትልቅ እምነት አስቀምጠው በፍላጎት ብቻ እንደገቡበት የሚናገሩት አቶ አርጋው፤ እርሳቸው ሲበሳጩ ሚስታቸው እየደገፈቻቸው፤ ሚስታቸው ሲከፉ ደግሞ ተስፋ እየሆኗቸው የጀመሩትን ለመቀጠል ይተጋገዙ ነበር።

የበጎ ተግባር ሥራቸውን ለማከናወን ሲንቀሳቀሱ 2000 ዓ.ም ሚሊኒየም የሚከበርበት ወቅት ነበር። መንግሥትም ጎዳና ላይ ልጆች እንዳይኖሩ ከጎዳና የማንሳት ሥራ ይሠራ ስለነበር ፍላጎታቸው ከመንግሥት እቅድ ጋር የተስማማ ሆኖ አገኙት። ሀዋሳ ከተማ ላይ ቤት ተከራዩ። በተለያየ ምክንያት ወደ ጎዳና የወጡ ልጆችንም ሰብስበው በተከራዩት ቤት ውስጥ በማኖር የሚያስፈልጋቸውም ነገር አሟልተው ለማስተማር እንቅስቃሴ ጀመሩ። በወቅቱም ከ8 አመት እስከ 17 አመት ዕድሜ ያላቸው 27 ልጆችን ነበር ከጎዳና ላይ ያነሱት።

አቶ አርጋው እንዳሉት፤ ልጆቹ ከባድ ሱስ ውስጥ የነበሩ በመሆናቸው ከሱስ አላቆ፤ ከመጥፎ ተግባራቸው መልሶ መልካም ዜጋ እንዲሆኑ ለማድረግ ፈታኝ ነበር። መማር የሚፈልገው ትምህርትቤት እንዲገባ፣ በአነስተኛ ንግድ ላይ መሰማራት የሚፈልግ ደግሞ እንዲሠራ እንደየፍላጎታቸው ለማገዝ ጥረት አደረጉ። ልጆቹ እንደፈለጉት ሊሆኑላቸው አልቻሉም። ከእነርሱ ይልቅ ጎዳና ላይ በነበሩ ጊዜ የሚያዟቸውን ነበር የሚሰሙት። በድብቅ ከእነርሱ ጋር ይገናኛሉ። አምጡ የሚሏቸውንም እየወሰዱ ይሰጧቸው ነበር። ልጆቹ ከቀድሞ ሕይወታቸው ሊቀየሩ አልቻሉም። በራሳቸው ጊዜም ወደነበሩበት ጎዳና ተመለሱ።

አቶ አርጋውና ባለቤታቸው ጎዳና ላይ የወጣን ሳይሆን መመለስ ሳይሆን፣ ወደ ጎዳና የሚያወጣቸውን ምክንያት ከምንጩ በማድረቅ ልጆችን መታደግ ወደ ሚለው ሥራ ገቡ። ልጆች ለምን ወደ ጎዳና እንደሚወጡ ለመገንዘብ ቻሉ። በብዛት ለጎዳና ተጋላጭ የሆኑባቸውን አካባቢዎችንም ለዩ። ልጆቹ በምግብ ማጣት ጎዳና እንደሚወጡ ካረጋገጡ በኋላ የትምህርትቤት ምገባ ማካሄድ ጀመሩ። ለዚህ ሥራቸውም መንግሥት አካባቢዎችንና ትምህርትቤቶችን በመለየት አግዟቸዋል። ሐመር፣ ምዕራብ አባያና ሲዳማ ውስጥ 31ሺ700 ልጆችን በመመገብ ነበር ሥራ የጀመሩት። ለአምስት አመት በዚህ መልኩ በመሥራት ልጆች ወደ ጎዳና እንዳይወጡ ታድገዋቸዋል።

በዚህ መካከል ሐመር አካባቢ የጥናት ሥራ ላይ የነበረ ወዳጃቸው በጎጂ ልማዳዊ ድርጊት የሚጎዱ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ልጆች መኖራቸውን ይነግሯቸዋል። በሐመር ሚንጊ በሚባለው ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ሕፃናት ይገደላሉ።ከወዳጃቸው በተሰጣቸው ሃሳብ መሠረት አካባቢው ላይ በመሄድ ልጆችን ለማትረፍ ተንቀሳቀሱ።

በወቅቱ በቦታው ሲደርሱ በሚንጊ የሚገደሉ እስኪወለዱ ድረስ የሚጠበቁ አስር እርጉዝ ሴቶችን ነበር ያገኙት። ከግድያ ለማትረፍ ይመለከታቸዋል ያሉትን አካላት በሙሉ ማነጋገሩን ተያያዙት። ግን እንዳሰቡት አላተረፏቸውም። ተቀባይነትም አላገኙም። በዚህም የተለያየ ተጽእኖ ደርሶባቸዋል።

ቁጭትም፤ እልህም፤ ስለያዛቸው ጥረታቸውን ቀጠሉ። በአጋጣሚ በአንድ ሰው እርዳታ ከመገደል ተርፈው የተጣሉ ሰባት ልጆችን ሰብስበው መረዳት ቻሉ። አሁን ላይ የተለያየ ጉዳት ያለባቸውን ጨምሮ የሚረዷቸው ቁጥራቸው ጨምሯል። 115 የሚሆኑት በተከራዩት ቤት ውስጥ የሚያግዟቸው ሲሆኑ፤ ከ60 በላይ የሚሆኑት ደግሞ በውጭ የተለያየ ድጋፍ የሚደረግላቸው ናቸው።

ከነዚህ ውስጥም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ተመርቀው ሥራ ይዘው እራሳቸውን መርዳት የጀመሩ፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት አባል የሆኑ ዜጎችን ማፍራት ችለዋል። እንዲህ ያለውን ሥራ የሚሠሩት በሀገር ውስጥም በውጭም የተለያዩ ሰዎችን ድጋፍ በመጠየቅ ነው።

አሁን ከሚረዷቸው በላይ ለማገዝ የቦታ ጥያቄ ከፍተኛ ፈተና ሆኖባቸዋል። ለገቢ ምንጭና ድጋፍም ለሚያደርግላቸው መኖሪያ የሚሆን ሕንፃ በመገንባት እነርሱ ባይኖሩ እንኳን ድጋፉ ዘላቂ እንዲሆን ፍላጎቱ ቢኖራቸውም ተባባሪ ባለማግኘታቸው ውስን ሰዎችን በቤት ኪራይ ውስጥ ለመርዳት መገደዳቸውን ነው አቶ አርጋው የሚናገሩት። የሚችሉትን ከማድረግ ወደኋላ እንደማይሉ ግን ተናግረዋል።

በግለሰብ ደረጃ የሚሠሩት በጎ ሥራ ተጽእኖ መፍጠር ቢችልም፤ ለሀገራዊ ችግር መፍትሔ የሚሆን ነገር ግን መፍጠር እንዳልቻሉ የሚሰማቸው አቶ አርጋው ከበጎ አድራጎት ሥራው የመነጨ ሌላ በጎ ሥራም ፈጥረዋል። ሰላም ከሰፈነ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ችግሮች ይፈታሉ የሚል እምነት አላቸው። ዜጎች ሃሳብ የሚያዋጡበት የሰላም ባንክ እንዲኖር እየተንቀሳቀሱ ነው።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ዓላማው በሀገር ሰላም እንዲኖር ነው። የሰላም ባንኩ ሀገር አሁን ከምትገኝበት ችግር እንድትወጣ የሚያስችል የእርቅ፣ የፍቅር፣ የአንድነት ሃሳብ ሁሉም ዜጋ እንዲያዋጣ ዕድል የሚያመቻች ነው። በተለይም ጎረቤት ከጎረቤቱ ሰላም መፍጠር ከቻለ ሀገር ሰላም ትሆናለች ይላሉ። በሰላም ባንኩ አማካኝነት የማኅበረሰብ የጋራ ውይይት መድረክ በማዘጋጀትና በተለያየ መንገድ ነው ሥራውን ለመሥራት ነው ያቀዱት። ማኅበረሰብን ከማኅበረሰብ ሊያቀራርብ የሚችል በቀን ተሰይመው የሚታወሱ መርሐግብሮች እንዲኖሩም ለማድረግ ነው ፍላጎታቸው።

ለአብነትም የመታረቅ፣ የጎረቤት ቀን እያለ በየቀኑ የሚካሄዱ መርሐ ግብሮች በተከታታይ ይተገበራሉ። ሥራውን ለመሥራት የሚያስችላቸው ፈቃድ ከማግኘት ጀምሮ የቅድመዝግጅት ሥራዎች እየተጠናቀቁ መሆናቸውን ነግረውናል። መላው ማኅበረሰብ የዚህ የሰላም ባንክ አካል እንዲሆን ነው ፍላጎታቸው። ‹‹ሰላም የሁሉም ፒኤልሲ መሆን አለበት›› ይላሉ።

ሰላም ባንክ በውስጡ ብዙ ሥራ እንዳለውና የመንግሥት እገዛም እንደሚያስፈልጋቸው ተናግረዋል። የውስጥንም የውጭ ጠላቶችን ለማሸነፍም ያግዛል ብለው ያምናሉ።

አቶ አርጋው አየለ የአቤነዘር ሰፖርቲቭ ኤንድ ዲቨሎፕመንት አሶሴሽን መሥራች እንዲሁም የግሎባል ፒስ ባንክ ሃሳብ አፍላቂና ሥራ አስኪያጅ ናቸው። እርሳቸው የመሪነቱን ሚና ይወጡ እንጂ ባለቤታቸውና ልጆቻቸው ከጀርባቸው እንደሚያግዟቸው ነው የነገሩን።

ስለልጆቻቸውም እንደነገሩን፤ ልጆቻቸው የወላጆቻቸውን ሃሳብ የሚደግፉና የሚያግዙ ናቸው። ውጭ ሀገር የመኖር ቀርቶ ረዘም ላለ ጊዜ እንኳን ለመቆየት ፍላጎት የላቸውም። ልጆቻቸው የሚኮሩባቸውና ሥራውንም እንደሚያስቀጥሉ ይተማመኑባቸዋል።

ልጆቻቸው ከሚረዷቸው ልጆች ጋር ቤተሰብ ሆነው ያደጉ በመሆናቸው ከሌላው ማኅበረሰብ ጋር መልካም የሆነ ማኅበራዊ ግንኙነት እንዲኖራቸው ያስቻላቸው መሆኑም አቶ አርጋው አጫውተውናል።



# ከኅብረቱ ጉባኤ ምን አተረፍን?

**ዳግም ከበደ**



የ37ተኛው የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ በመዲናችን አዲስ አበባ ለቀናት ሲካሄድ ቆይቶ በስኬት መጠናቀቁን የኢትዮጵያ መንግሥት ይፋ አድርጓል። ጉባኤው የኅብረቱን አባላት አጀንዳ ከማሳካት ባሻገር አዘጋጅ ሀገር ለሆነችው ኢትዮጵያ በርካታ ድሎችን አስመዝግቦ ያለፈ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ጉባኤው ከመካሄዱ በፊት የተሳታፊዎችን ደህንነት ከመጠበቅ፣ ከመስተንግዶና የኢትዮጵያን መልካም ገፅታ የሚገነቡ የቱሪዝም መስህቦችን ከማስተዋወቅ አንፃር ቅድመ ዝግጅቶች ሲደረጉ ነበር። ጉባኤው ከተጠናቀቀ በኋላ በእቅድ የተቀመጡትን ግቦች በማሳካት ድሎች መመዝገባቸውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ይፋ አድርጎ እንደነበር ይታወሳል።

«37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ኢትዮጵያ የተከበረችበትና የተመሰገነችበት ነው» በማለት ከጉባኤው ማግስት የተገኙ ድሎችን ይፋ ያደረጉት አምባሳደር ብርቱካን አያኖ ዋናው የመሪዎች ስብሰባና ቀደም ሲል የነበሩ ስብሰባዎች በስኬት መጠናቀቃቸውን አብስረዋል። ኢትዮጵያም ይህንን ተከትሎ የተከበረችበትና የተመሰገነችበት መሆኑን ያነሱት አምባሳደር ብርቱካን፣ ጉባኤው ያለምንም የጸጥታ ችግር የተጠናቀቀ እንደነበር አንስተዋል። እንግዶች በክብር መጥተው በክብር ተሸኝተዋል። በየአመቱ እንግዶች አዳዲስ ነገር እንዲያውቁና እንዲለምዱ ችለዋል፣ በቀጣይም ከፍ ባለ ሁኔታ ለመቀበል ዝግጅት እንደሚደረግም ይፋ አድርገዋል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ በስኬት እንዲጠናቀቅ ቀደም ብሎ ለሦስት ወራት ሲካሄድ ነበር። በዚህም 35 የሚደርሱ ተቋማት ተሳትፈውበታል። እንግዶችን ለመቀበል በሌሎች ሀገራት ያልተለመዱ የእንግዳ አቀባበል ዝግጅት መደረጉንም እነዚሁ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም ኢትዮጵያን ያስከበረና በልዩነት የታየ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከጉባኤው ማግስት አሳውቋል።

በስብሰባ ቱሪዝም እንዲሁም ታላላቅ ጉባኤዎች ለሀገራት ስለሚኖራቸው ተያያዥ ጥቅሞች በተደጋጋሚ ሲናገሩ የሚደመጡት ምሁራን የአፍሪካ ኅብረትን የመሰሉ ዓለም አቀፍ ሁነቶች የሀገርን ገፅታ ለመገንባት፣ ቱሪዝምን ለማሳደግ እንዲሁም መሰል ዝግጅቶችን በተመራጭነት ለማሰናዳት ትልቅ ዕድል የሚከፍቱ መሆናቸውን ይናገራሉ። የዘንድሮው የኅብረቱ ጉባኤ በስኬት መሰናዳትም የዚሁ ማሳያ እንደሚሆን ይገመታል። እንደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መረጃ ከሆነ በ37ተኛው የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ እንግዶች በተደረገላቸው አቀባበል እንግዶችም ደስተኛ መሆናቸውና ምስጋና ማቅረባቸው ታውቋል። ሚኒስትሮችም እንግዶችን ሲቀበሉና ሲሸኙ ስለ ኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ በማስረዳትና በማስተዋወቅ እንደነበር ተገልጿል።

የዝግጅት ክፍላችን 37ተኛው የኅብረቱ ጉባኤ ከመካሄዱ ሁለት ሳምንታት አስቀድሞ «ኢትዮጵያ ከቱሪዝምና ከሀገር ገፅታ ግንባታ አኳያ ዕድሉን በምን መልኩ ልትጠቀምበት ትችላለች» የሚል ጥያቄ አቅርቦ ሰፋ ያለ ዳሰሳ ማቅረቡ ይታወሳል። ጉባኤው ከተጠናቀቀ በኋላ ደግሞ «የታቀዱት ግቦች ከምን ደረሱ፤ ምን ዓይነት ስኬቶችስ ተመዘገቡ» በማለት ጥያቄውን ብሔራዊ ኮሚቴ ውስጥ በቀዳሚነት ተሳታፊ ወደነበረው ቱሪዝም ሚኒስቴር ይዞ ቀርቦ ነበር። በምላሹ በሚኒስቴር መሥሪያቤት ውስጥ የስትራቴጂክ ዩኒት አስተባባሪ የሆኑት አቶ ቴዎድሮስ ደርበው እንደሚከተለው ምላሽ ሰጥተውበታል።

እርሳቸው እንደሚሉት ጉባኤው ከመካሄዱ ሦስት ወራት ቀደም ብሎ ብሔራዊ ኮሚቴ ተዋቅሮ ልዩ ልዩ ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተው ነበር። በዚህም ኢትዮጵያ የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤን የማዘጋጀት ዕድል ስላላት ይህንን መልካም አጋጣሚ ለብሔራዊ ጥቅም በሚያግዝ መልኩ ለማሰናዳት ዝግጅቶች አድርጋ ነበር። በተለይ ቱሪዝምን ለማሳደግ፣ ለማስተዋወቅና በገበያ ልማትና ድርሻ ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን አጋጣሚ የሚፈጥር እንደሆነ ታምኖበት ከዚህ ለማትረፍ በርካታ እቅዶች ተይዘው እንደነበር ያስታውሳሉ።

በጉባኤው በርካታ ቁጥር ያላቸው የአፍሪካ ሀገራት መሪዎችና የተለያዩ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች ተሳታፊ መሆናቸውን ያነሱት አቶ ቴዎድሮስ ደርበው፤ እንግዶቹ የሚስተናገዱባቸው ሆቴሎችና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሀገርን ስም በመልካም ሊያስጠራና የሀገርን ገጽታ የሚገነባ ጥራት ያለው አገልግሎት ማቅረባቸውንና በዚያም ስኬት መገኘቱን ያነሳሉ። ሆቴሎቹ ለጉባኤው ተሳታፊዎች ጥሩ ትዝታን የሚጥል የኢትዮጵያን መልክ የሚያሳይ መስተንግዶ መስጠታቸውንና በዚያም ስኬት መገኘቱን ይናገራሉ።

ለዚህ ስኬት መገኘት የቱሪዝም ሚኒስቴር ቀደም ብሎ ከሆቴሎች ጋር በመነጋገር እና ቅድመ ገለፃዎችን በመስጠት ፍፃሜው እንዲያምር በርካታ ሥራዎች መሥራቱን የሚያነሱት አቶ ቴዎድሮስ ደርበው፤ ለተሻለ ስኬት መመዝገብ አስቀድመው የተሠሩት ቅድመ ዝግጅቶች አስተዋፆ እንደነበራቸው ተናግረዋል። ከሆስፒታሊቲው ባሻገር በኅብረቱ ግቢ ውስጥ ሌሎች ተያያዥ ሥራዎች መሠራታቸውን በመግለፅም የኢትዮጵያ ዋንኛ መገለጫ የሆነውን ባህላዊ የቡና ማፍላት ሥነሥርዓት ማስተዋወቅ መቻሉን ተናግረዋል።

ስብሰባው በሚካሄድበት የኅብረቱ ግቢ ውስጥ የኢትዮጵያን መገለጫዎች የማስተዋወቅ ሥራ መከናወኑን የሚናገሩት አቶ ቴዎድሮስ ደርበው፣ ይህም ዋና ዋና የኢትዮጵያ ምልክቶችን ለአፍሪካውያንና ዓለም አቀፍ ዲፕሎማቶች በሚገባ ማሳየት የተቻለበት አጋጣሚ የፈጠረ እንደሆነ ይገልፃሉ። ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ (ምድረ ቀደምት) መሆኗን የሚያሳዩ የተለያዩ ማስታወቂያዎችና ግንዛቤ መስጫ ሁነቶች ተካሂደዋል የሚሉት ስትራቴጂክ ቡድን መሪው ምድረ ቀደምትነቷን ከሚያሳዩ መገለጫዎች ውስጥ አንዱ ማስረጃም የቡና መገኛ መሆኗ እንደሆነ ይናገራሉ።

«ሌላው ምድረ ቀደምትነቷን አስረግጦ የሚያሳየው ማስረጃ ኢትዮጵያ የዓባይ ወንዝ መፍለቂያና መነሻ መሆኗ ነው» የሚሉት የስትራቴጂክ ቡድን መሪው አቶ ቴዎድሮስ ደርበው፤ እነዚህ ሦስት አስረጂ ሀብቶችን የኅብረቱ ጉባኤ በሚካሄድበት ስፍራ በመጠቀም ብራንዱን (ምድረ ቀደምት) የማስተዋወቅ ሥራ መከናወኑን ይናገራሉ።

በወቅቱ በኅብረቱ ስብሰባ መሪዎች፣ ዲፕሎማቶች፣ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃንና ሌሎች ባለድርሻዎች በብዛት እንደተገኙ የሚገልፁት አቶ ቴዎድሮስ፤ ሁሉም ስለ ኢትዮጵያ እንዲያውቁ ብሎም በርካታ የመስህብ ሀብቶች መገኛ እንደሆነች እንዲረዱ ለማድረግ መቻሉን ይናገራሉ። ሂደቱም አጋጣሚውን ተጠቅሞ የኢትዮጵያን ገፅታ መገንባት እንዲቻል የተደረገበት መሆኑን ያስረዳሉ።

የቱሪዝም ዘርፍን ለማሳደግ የመጀመሪያው እርምጃ ስለ መስህብና ሀብቶች መረጃ መስጠት ቀዳሚው ተግባር መሆኑን የሚያነሱት አቶ ቴዎድሮስ፤ አንድ ጎብኚ ወደ ኢትዮጵያ ቢመጣ ምን ዓይነት አገልግሎቶችን፣ የመስህብ ስፍራዎችን፣ የታሪክና የመዝናኛ ቦታዎችን በምን መንገድ ማግኘት እንደሚችል መረጃ መስጠት ያስፈልጋል ይላሉ። የኅብረቱ ስብሰባ ለአጭር ጊዜም ቢሆን የተገኙ እንግዶችም ይህ መረጃ እንዲኖራቸው በማስቻል በመዲናዋ አዲስ አበባ ውስጥ ያሉ መስህቦችን እንዲያውቁና ያላቸውን ጥቂት ጊዜ ተጠቅመው እንዲመለከቱት መደረጉን ይናገራሉ።

«በአፍሪካ ኅብረት ስብሰባ ላይ የተገኙ ሁሉም የኢትዮጵያን መስህብ ስፍራዎች ላይጎበኙ ይችላሉ» የሚሉት አቶ ቴዎድሮስ ወደፊት ጊዜ ሲኖራቸው ግን በእቅድ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ በቂ መረጃ እንዲኖራቸው እነርሱንም ታሳቢ በማድረግ የማስተዋወቅ ሥራ መከናወኑን ይናገራሉ። በኢትዮጵያ ቆይታ አድርገው ሲመለሱም ስለ ሀገሪቱ መልካም እይታ እንዲኖራቸውና ለወዳጅ ዘመዶቻቸው ለማጋራት ዕድሉ ሊፈጠር ስለሚችል የገፅታ ግንባታ ሥራ መከናወኑን ያስረዳሉ።

የአፍሪካ ኅብረት ስብሰባ በሚካሄድበት ወቅት ጎን ለጎን የኢትዮጵያን የቱሪዝም ዘርፍ ሊያሳድጉ የሚችሉ የማስተዋወቅና የገፅታ ግንባታ ሥራዎች ይደረጋሉ የሚሉት አቶ ቴዎድሮስ፤ ዘንድሮው በተመሳሳይ በዝግጅት ኮሚቴ ውስጥ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አባል በመሆን በተመሳሳይ ዘንድሮም ተግባራዊ ሥራዎች መካሄዳቸውን ያነሳሉ። ይሁን እንጂ ከዚህም በበለጠ ወደፊት የጎንዮሽ ዝግጅት በመፍጠር የበለጠ በቱሪዝም ኢትዮጵያን ተጠቃሚ የማድረጉ ተግባር ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ ይናገራል።

የኅብረቱ ስብሰባ በርካታ ተሳታፊዎች ያሉትና ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃንም ሽፋን የሚሰጡት መሆኑን የሚያነሱት አቶ ቴዎድሮስ ይህንን ዕድል በቀላሉ ማየት እንደማይገባ ይገልፃሉ። በመጪዎቹ መሰል ዝግጅቶች ላይ የኢትዮጵያን ቱሪዝም የሚያሳድጉ፣ የሚያስተዋውቁ አሳታፊ ዝግጅቶችን መፍጠር እንደሚያስፈልግም ያነሳሉ። የአፍሪካ ኅብረት ስብሰባ ቋሚ እንደመሆኑ አጋጣሚውን መጠቀም እንደሚያስፈልግ በማንሳት የኢትዮጵያን ባህል፣ ታሪክ፣ ቅርስ፣ ተፈጥሮና ሌሎች ልዩ ልዩ ሀብቶችን ማስተዋወቅ የሚያስችል የቱሪዝም የጎንዮሽ ሁነት በቋሚነት ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ። ለዚህም እንደ ሚኒስቴር መሥሪያቤት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ያነሳሉ።

አቶ ይታሰብ ስዩም የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ናቸው። እርሳቸው «በቀጣይ ከዚህ መሰል አጋጣሚ ኢትዮጵያን በምን መልኩ ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል» በሚለው ጉዳይ ላይ ሃሳባቸውን ይሰነዝራሉ። በዚህም የሆስፒታሊቲ ዘርፉ ተዋንያን እንዲሁም በቱሪዝም ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ባለድርሻዎች የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ ሲደርስ ብቻ ሳይሆን ሁሌም ዝግጁ ሆነው መጠበቅ እንዳለባቸው ይገልፃሉ። የይድረስ ይድረስ ዝግጅት የኢትዮጵያን የማይስ ቱሪዝም እና የቱሪስት ፍሰቱን እንደማያሳድገው በማንሳትም ሁል ጊዜም ቢሆን ሆቴሎችና የመስህብ ስፍራዎች ለውጥና የማያቋርጥ እድገት ማምጣት እንደሚጠበቅባቸው ያነሳሉ። የትምህርትና ሌሎች ባለድርሻ አካላትም ድጋፍና ክትትል ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ያነሳሉ።

እንደ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን የጠበቁ ስብሰባዎችን በማዘጋጀት እንደሚገኝ የማይስ ቱሪዝም ዘርፍ ተጠቃሚ ለመሆን ዕድሉን የሚከፍት ልምድ ለማዳበር እንደሚጠቅም ይናገራሉ። ይሁን እንጂ መሪዎች የሚገኙበት እና በኅብረቱ ጽሕፈት ቤት የሚደረግ ጉባኤ ከመሆኑ አኳያ ከደህንነትና ጥበቃ አንፃር ጥበቃ የሚደረግበት መሆኑን ነው የገለጹት። ይህ አጋጣሚ ልክ እንደሌሎቹ ጉባኤዎች ነፃነት የሚሰጥ ባይሆንም ጎን ለጎን በሚካሄዱ ዝግጅቶች መሪዎችን፣ ዲፕሎማቶችን እና ልዑካኑን ስለ ኢትዮጵያ መስህቦች እንዲያውቁ ዕድል መፍጠር አስፈላጊና የግድ እንደሆነ ጠቅሰው፤ ይህን ማድረግ ከተቻለ የኢትዮጵያን ገፅታ ከመገንባት ባሻገር ቱሪዝም ሀብቶችን ማስተዋወቅ እንደሚያስችል ያስረዳሉ።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ማይስ ቱሪዝም (ስብሰባዎችን መሠረት አድርገው የሚካሄዱ የቱሪዝም ሁነቶች) አንድ ትሪሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚያንቀሳቅስ ግዙፍ ኢንዱስትሪ እንደሆነ ነው። ይህ አሃዝ እስከ 2025 (ከሁለት ዓመታት በኋላ) ወደ አንድ ነጥብ 5 ትሪሊዮን የአሜሪካ ዶላር እንደሚመነደግ ቅድመ ግምቱን አስቀምጧል። ከዚህ መረዳት የምንችለው የሆቴል፣ ኮንፍረንስ፣ ኤግዚቢሽንና ባዛር እንዲሁም ልዩ ልዩ የማይስ ቱሪዝም ንዑሶችን የሚይዘው ኢንዱስትሪ ለዓለማችን የምጣኔ ሀብት ምንጭ እንደሆነ ነው። ለዚህ ነው በዘርፉ ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ ምሁራን ኢትዮጵያ የአፍሪካ ኅብረትን ጨምሮ ታላላቅ ዓለም አቀፍ ሁነቶችን በማዘጋጀት ተጠቃሚ መሆን አለባት በማለት የሚሞግቱት።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## ሉዓላዊነትን የገነባው የሰማዕታቱ አፅም

**ዋስልኝ አየለ**

የየካቲት ወር በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በተለይም በታሪክና ፖለቲካ ጉልህ ሚና ያለው ወር ነው። ከእነዚህ የየካቲት ወር ጉልህ ታሪካዊ ክስተቶች የካቲት 12 የሰማዕታት ቀን እና ዓድዋ በደማቁ የሚታወሱ ናቸው። ዓድዋን በቀኑ ስንደርስ እናስታውሰዋለን።

ለዛሬው ከ87 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ስለተከሰተው የሰማዕታት መታሰቢያና መነሻ ሰበቦቹን እናስታውሳለን። ከዚያ በፊት እንደተለመደው ሌሎች የዚህ ሳምንት ክስተቶችን እናስታውስ።

ከ49 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት የካቲት 11 ቀን 1967 ዓ.ም ኢትዮጵያን ለ27 ዓመታት ያህል ከመሩት የኢህአዴግ ግንባር ድርጅቶች አንዱ እና ግንባር ቀደሙ የሆነው ሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) ተመሠረተ።

ከ12 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ.ም በኢትዮጵያ ባህልና ወግ ውስጥ በአደባባይ የማይደፈሩ ወሲባዊ ቃላትን በመጠቀም የሚታወቀው ደራሲ ስብሃት ገብረእግዚአብሔር አረፈ። ደራሲ ስብሃት ገብረእግዚአብሔር ወሲባዊ ቃላትን በመጠቀም ስሙ ተደጋግሞ ይነሳ እንጂ ማኅበራዊና ታሪካዊ ጉዳዮችንም የጻፈ ደራሲ ነው። በግል ሕይወቱ ለየት ያለ ፍልስፍና የሚከተለው ስብሃት ገብረእግዚአብሔር በአስቂኝ ፍልስፍናዊ መልሶቹም ይታወቃል።

ከ28 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት የካቲት 14 ቀን 1988 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፓርላማ ደርግ መጋቢት 28 ቀን እንዲከበር አድርጎት የነበረውን የአርበኞች ቀን በመሻር ሚያዝያ 27 ቀን እንዲከበር ወሰነ።

ከ100 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት የካቲት 16 ቀን 1916 ዓ.ም ኢትዮጵያዊው የመጀመሪያው አፍሪካዊ «የንግድ ጄት» አብራሪ የሆኑት ኢትዮጵያዊው ካፒቴን ዓለማየሁ አበበ ተወለዱ።

ከ88 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት የካቲት 16 ቀን 1928 ዓ.ም ደራሲ፣ የሥነ ጽሑፍ መምሕር፣ ገጣሚ እና የተውኔት ጠቢብ ዳኛቸው ወርቁ ተወለደ።

ከ87 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት፤ ከየካቲት 12 ጭፍጨፋ 4 ቀናት በኋላ፣ የካቲት 16 ቀን 1929 ዓ.ም ፀረ ፋሺስት አርበኞቹ እና ሀገር አስተዳዳሪዎቹ የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ አማቾች ራስ ደስታ ዳምጠው እና ደጃዝማች በየነ መርዕድ በፋሺስት ኢጣሊያና በባንዳ ወታደሮች ተገደሉ።

በዚሁ ወደ የካቲት 12 ሰማዕታት ታሪክ እንሂድ።

በ1888 ዓ.ም በዓድዋ ላይ ዓለም አቀፍ ውርደትን የተከናነበው ጣሊያን ለ40 ዓመታት ያህል ያኔ የደረሰበት ሽንፈት ሲያንገበግበው ከኖረ በኋላ በ1928 ዓ.ም በቀሉን ሊወጣ ዳግም ወደ ኢትዮጵያ መጣ።

እነሆ ከ87 ዓመታት በፊት የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም እንዲህ ሆነ። ከጣሊያን ንጉሣዊ ቤተሰቦች አንድ ልዑል ልጅ በመወለዱ በኢትዮጵያ ድል ያለ ድግስ ተዘጋጅቶ እንዲከበር በጀኔራል ግራዚያኒ ትዕዛዝ ተላለፈ። ዝግጅቱም በቀድሞው የገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት (በአሁኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) ቅጥር ግቢ ውስጥ የፋሽስቱ ባለሥልጣናት እና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው ሁሉ እንዲገኙ ተደረገ።

በዚህ ዝግጅት ላይ ትልቅ የደስታ ስጦታ መዘጋጀቱን አብርሃም ደቦጭ ሰማ። ውሳኔውንም ለበጅሮንድ ለጥይበሉ ገብሬ፣ ለብላታ ዳዲ፣ ለቀኝ አዝማች ወልደዮሐንስ፣ ለደጅ አዝማች ወልደ አማኑኤል እና ሌሎች ኢትዮጵያውያን ጓደኞቹ ተናገረ። ጥሪው ከተደረገበት ቦታ ማንም ሰው መሄድ እንደሌለበትም አስታወቃቸው። ዳሩ ግን የፋሽስቱ እንዲህ በሀገራቸው ላይ ደጋሽ እና ጋባዥ መሆን ያላንገበገባቸው ሆድ አደሮች «ዞር በል ወዲያ» ብለውት ለመሄድ ወሰኑ። አብርሃምም ለቅርብ ጓደኛው ለሞገስ አስገዶም ከነገረው በኋላ ምን ማድረግ እንዳለባቸው መከሩ። በዚች ታሪከኛ ቀን የካቲት 12 ከማንም ቀድመው ዝግጅቱ ላይ መገኘት እንዳለባቸውም ወሰኑ።

ከመሄዳቸው በፊትም እንዲህ አደረጉ። በአብርሃም ደቦጭ ቤት ውስጥ የጣሊያንን ባንዲራ በሳንቃ ወለል ላይ አንጥፈው ሚስማር ገደገዱበት። የጣሊያን ፋሽስት ጉዱን አላየ! እዚያ ሸር ጉድ ይላል። አብርሃም እና ሞገስም የልባቸውን በልባቸው ይዘው ወደ ዝግጅቱ ገቡ።



**የካቲት 12 የሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት፣**

ግራዚያኒም በአዳራሹ እየፈነጠዘ ብሉልኝ ጠጡልኝ ይል ጀመር። አዳራሹ ውስጥ ታድመው ዝግጅቱን ከሚያደምቁ አድር ባዮች ውስጥ ግን፤ የድግሱ ምግብ እሬት እሬት ያላቸው፣ አዳራሹ የፋሽስት ሶላቶ መራገጫ መሆኑ ያንገበገባቸው የሀገር ነፃነት የናፈቃቸው ሁለት ወጣቶች ነበሩ። ሞገስ አስገዶም እና አብርሃም ደቦጭ። ገዳይ ቢያረፋፍድ ሟች ይገሰግሳል እንደሚባለው፤ ግራዚያኒ ከሚገባው በላይ ቅጡን አጣ። በአዳራሹ የታደመውን ሰው እየዞረ ለተወለደው ልጅ ስም እንዲያወጡ ጠየቀ። አድር ባይ ባንዳ ሁሉ ያስደስታል ያለውን ስም ያወጣ ጀመር። አሁን የአብርሃምና የሞገስ ትዕግስት አልቋል። ለማንም የፋሽስት ዲቃላ ማነው ስም የሚያወጣ ተባባሉ። በቃ አሁን ጉድ ሊፈላ ነው! በኪሳቸው ደብቀውት የነበረውን ቦንብ መዥረጥ፣መዥረጥ አደረጉት። ግራዚያኒ ላይ ተወረወረ። ቆስሎም ወደቀ። ለአሸሸ ገዳሜ የታሰበው አዳራሽ «ዋይ! ዋይ!» ተባለበት።

የጣሊያን ፋሽስቶች በእልህ እና በብስጭት ከሰላሳ ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያንን በግፍ ጨፈጨፉ። አብርሃም ደቦጭ እና ሞገስ አስገዶምም ወደ ሱዳን እየሄዱ ሳሉ ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች ተገደሉ። ከዚያ በኋላ እንግዲህ የኢትዮጵያ ቆራጥ አርበኞች ጣሊያንን ከሀገር ለማስወጣት ሴት ወንድ ሳይሉ በዱር በገደሉ መዋጋት ጀመሩ። እነ ሸዋረገድ ገድሌ እና ከበደች ሥዩም ከሴት አርበኞች የሚጠቀሱ ናቸው።

የሞገስ አስገዶምና የአብርሃም ደቦጭ ቁርጠኛ ውሳኔ ብዙ ጀግኖችን ለትግል አነሳሳ። በኋላም ለእናት ሀገራቸው ቆርጠው በተነሱ አርበኞች ትግል የጣሊያን ፋሽስት ጓዙን ጠቅልሎ ከኢትዮጵያ ወጣ። እነዚህ ጀግኖች አጥንታቸውን ከስክሰው ደማቸውን አፍስሰው እነሆ ኢትዮጵያን ብቸኛ አፍሪካዊት ነፃ ሀገር አስብለዋታል።

ጣሊያኖች ደጋግመው የሞከሩት ሙከራ በኢትዮጵያውያን ጀግኖች ከሽፏል። ጣሊያን በ1879 ዓ.ም ዶጋሌ ላይ፣ ከዘጠኝ ዓመታት በኋላ ደግሞ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ዓድዋ ላይ ሽንፈትን አስተናግዳለች። ይህ ሁሉ የኢትዮጵያ ድል ነው። በመጨረሻም በየካቲት 12 ሰማዕታት ምክንያት የኢትዮጵያ አርበኞች ዳግም የሀገራቸውን ነፃነት አስጠበቁ። ለዚህም መታሰቢያ ከአምስት ኪሎ ከፍ ብሎ ስድስት ኪሎ ሳይደርስ የሚገኘው የካቲት 12 የሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት ተገነባ።

በጭፍጨፋው ሕይወታቸውን ያጡ ዜጎችን ለመዘከር የካቲት 12 በብሔራዊ ደረጃ እንዲዘከር በ1934 ዓ.ም ታወጀ። በ1951 ዓ.ም ደግሞ አሁን የምናየው እና 28 ሜትር ርዝመት እንዳለው የሚነገረው የሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት እንዲቆም ተደርጓል።

የነገሩን ሥረ መነሻ ካየነው ከዓድዋ በፊትም ቆየት ያለ ነው። አውሮፓውያን የአፍሪካ ሀገራትን ለመቀራመትና የቅኝ ግዛት ለማድረግ ዓይናቸውን ወደ አፍሪካ ያማተሩበት የታሪክ ምዕራፍ ነበር። በወቅቱ አብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገራት በአውሮፓውያን እጅ ሲወድቁ፣ ኢትዮጵያን ለመውረር ቀይ ባሕርን ያቋረጠችው ጣሊያን ግን ሳይሳካላት ቀርቷል። በነጮቹ የእርስ በርስ ተባባሪነት ተደጋጋሚ ሴራ ቢሞክሩም ኢትዮጵያ ላይ ግን ሊሠራ አልቻለም።

ይህ ተደጋጋሚ ሙከራ ሲከሽፍ ቆይቶ በ1888 ዓድዋ ላይ የኢትዮጵያን ገናናነት ከፍ አድርጎ ያሳየው ታላቁ የዓድዋ ድል ተመዘገበ። በጦርነቱም፤ የጣሊያንን ጦር የገጠመው የኢትዮጵያ ሠራዊት ጣሊያንን በማሸነፍ ድል ማስመዝገቡ፣ ድሉ የዓለም ጥቁር ድል ሲባል ጣሊያን የሽንፈት ካባ ተከናንባ የኢትዮጵያን ምድር ለቃ ወጣች።

በዚህ በዓድዋ ሽንፈት ቂም የያዘችው ጣሊያን ከ40 አመታት የሰፌ ዝግጅት በኋላ ተመልሳ በመምጣት ኢትዮጵያን በመውረር ብዙ ኢትዮጵያውያንን ለመስዋዕትነት በመዳረጓ የካቲት 12 የዚያ መስዋዕትነት መታሰቢያ ሆነ። የታሪክ ምሁሩ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ እንደሚሉት፤ ጣሊያን ለ40 ዓመታት ያህል ከፍተኛ ዝግጅት ስታደርግ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ግን ከፍተኛ መዘናጋት ነበር። በሕዝቦቿ ጀግንነትና አይበገሬነት ድል ማድረግ ተቻለ እንጂ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል የነበረው ሁኔታ የታሰበበት አልነበረም።

በተለይም ከዳግማዊ አጼ ምኒልክ ህልፈት በኋላ የነበረውን የኢትዮጵያ ታሪክ ካየነው ደግሞ እንደ ሰገሌ ዓይነት የእርስ በርስ ጦርነቶችና ሽኩቻዎች የነበሩበት ነው። አልጋ ወራሹ ተፈሪ መኮንን ንጉሠ ነገሥት እስከሚሆኑ ድረስ የነበሩ ሁኔታዎችም ወጣ ገባ ያሉ ነበሩ። ይፋዊው የጣሊያን ወረራ ንጉሠ ነገሥቱ ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ መንበረ ሥልጣናቸውን ካረጋጉ በኋላ መሆኑ ግን የተሻለ ሳያደርገው አይቀርም፤ ምክንያቱም ንጉሡ ብዙ የዲፕሎማሲ ሥራ መሥራታቸው ይነገርላቸዋል።

ይፋዊው የጣሊያን ወረራ በተመጀመረ ጊዜ ደግሞ የዓለም መንግሥታት ማኅበር (League of Nations) የተመሠረተበት ነበር፤ ኢትዮጵያ ለዚሁ ማኅበር ወረራው ተገቢ አይደለም በማለት በንጉሷ በኩል አቤት ብትልም አጋርነት ካሳዩ ጥቂት ሀገራት ውጪ ሰሚ አላገኘችም ነበር።

ይሁንና የዓለም መንግሥታት ማኅበር (league of nations) ከተመሠረተ ከዓመታት በኋላ ጣሊያን በድጋሚ ኢትዮጵያን ለመውረር ጦርነት ጀመረች። በወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥትና አርበኞች ሀገርን ላለማስደፈር ከፍተኛ ተጋድሎ አድርገዋል።

ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ የጣሊያንን ድርጊት አዲስ ለተቋቋመው የመንግሥታት ማኅበር ለማመልከት ወደ ውጭ ሀገራት ቢሄዱም ሕግና ሉዓላዊነት በወቅቱ ትኩረት ሊሰጣቸው ስላልቻለ ኢትዮጵያውያን የነፃነት ተጋድሏቸውን አጠናክረው ቀጠሉ ማለት ነው። ስለዚህ የየካቲት 12 ሰማዕታት ጀግኖች እልቂት የዓለም ኢፍትሐዊነትና አድሎ የፈጠረው ጭምር ነው። ምንም እንኳን ኢትዮጵያውያን በጀግንነታቸው ቢኮሩበትም የዓለምን ኢፍትሐዊነት ግን ሲመሰክር ይኖራል።

ለአፍሪካ ሀገራት ቅኝ ግዛት መነሻ የነበረውን የበርሊን ጉባኤ በጥቂቱ እናስታውሰው። ፖርቱጋል በአውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር 1884 በፖርቱጋል ጥያቄ መሠረት የጀርመን ቻንስለር ኦቶ ቮን ቢስማርክ ዋናውን የምዕራባዊ ሀገሮች ዓለም አቀፋዊ ስብሰባ በመሰብሰብ ጥያቄዎችን በማደራጀት በአፍሪካ ሀገሮች ቁጥጥር ላይ ተወያዩ።

የበርሊን ኮንፈረንስ በተከፈተበት ጊዜ አሥራ አራት ሀገሮች በአምባሳደሮች ተገኝተዋል። በወቅቱ የተወከሉት ሀገሮች ኦስትሪያ ሃንጋሪ፣ ቤልጂየም፣ ዴንማርክ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ታላቋ ብሪታንያ፣ ጣሊያን፣ ኔዘርላንድ፣ ፖርቱጋል፣ ሩሲያ፣ ስፔን፣ ስዊድን፣ ኖርዌይ ቱርክ እና ዩናይትድ ስቴትስ ነበሩ። ከኅዳር 1884 ጀምሮ ለሦስት ወራት በተካሄደው ውይይት በአውሮፓውያን ታላላቅ ኃይሎች መካከል የስብሰባዎች ስብስብ ነበር። በድርድሩ ውስጥ የተሳተፉት ሀገራት ዋና ዓላማ የአፍሪካን ቅኝ ግዛት ለማስፈፀም ዓለም አቀፍ የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት ነበር።

ከአስራ አራቱ ሀገራት መካከል ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ታላቋ ብሪታንያ እና ፖርቹጋል በወቅቱ የቅኝ ግዛት አፍሪካን ተቆጣጠሩት።

በጉባኤው ጊዜ በአፍሪካ የባሕር ዳርቻዎች የሚገኙት የአውሮፓ ኃያላን ሀገሮች ብቻ ነበሩ። በበርሊን ጉባኤ ላይ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች የአፍሪካን አህጉራት ለመቆጣጠር እየተዋጉ ሁሉ ነበር። ቢሆንም ግን ከመዋጋታቸው ይልቅ ስምምነታቸው በልጦ አፍሪካን ተከፋፍለው ቅኝ ገዝተዋል። የአውሮፓ ቅኝ ገዥ ሀገራትና የአፍሪካ ቅኝ ተገዢ ሀገራት የሚከተሉት ነበሩ።

ታላቋ ብሪታኒያ የኬፕ ኤይ ካይሮን ቅኝ ግዛቶች ለማግኘት የግብፅ፣ የታላቋ ሱዳን፣ ኡጋንዳ፣ ኬንያ (የብሪቲሽ ምሥራቅ አፍሪካ)፣ ደቡብ አፍሪካ እና ዛምቢያ፣ ዚምባብዌ (ሩዴያ)፣ ቦትስዋና፣ ብሪታኒያ ናይጄሪያና ጋና (ጎልድኮስት) ገዝታለች።

ፈረንሳይ በአብዛኛው ምዕራብ አፍሪካን፣ ከሞሪታኒያ እስከ ቻድ (ፈረንሣዊ ምዕራብ አፍሪካ) እንዲሁም ጋቦንና ኮንጎ ሪፖብሊክ (ፈረንሳይ ኢኳቶሪያል አፍሪካ) ወስዳለች።

ቤልጂየም እና ንጉሥ ሌኦፖል ዲሞክራቲክ ኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ (ቤልጂየ ኮንጎ) ተቆጣጠሩት።

ፖርቱጋል በምሥራቅና በምዕራብ ሞዛምቢክ ሞዛምቢክን ወሰደች። የጣሊያን ይዞታዎች ደግሞ ሶማሊያ (ጣሊያን ሶማሊላንድ) እና የኢትዮጵያ ክፍል ነበሩ።

ጀርመን በናሚቢያ (ጀርመን ደቡብ ምዕራብ አፍሪካ) እና ታንዛኒያ (ጀርመን የምሥራቅ አፍሪካ) አግኝታለች።

የአንዳንድ አፍሪካ ሀገራት ስሞች በቅኝ ገዥዎቻቸው ስያሜ የወጡ ናቸው። ቅኝ ገዢዎቹ የያዙትን ቦታ የራሳቸውን ሀገር መነሻ ስም ያደርጉታል። በተለይ እንግሊዞች «ብሪቲሽ...» እያሉ ይሰይማሉ።

ይህ ሁሉ አፍሪካን የመቀራመት ዘመቻ ነው እንግዲህ ኢትዮጵያ ላይ ሲደርስ የከሸፈባቸው። ምንም እንኳን የሠሩት ሥራ ዛሬ ድረስ ያበለሻሸው ነገር ቢኖርም፤ ኢትዮጵያ ግን በራሷ ማንነት ብቻ የምትታወቅ የጀግና ሀገር እንድትሆን አድርጓታል። ይህ የሆነው ደግሞ እንደ የካቲት 12 ዓይነት የሰማዕታት ዋጋ ተከፍሎበት ነው።

ክብር ለጀግኖች ሰማዕታት!

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## ህልፈቱ ጥበብን ያጎደላት ጌታቸው

ቤዛ እሸቱ

አዲስ አበባ፣ የካ ሚካኤል ጌታቸው ጸጋዬ ይሄን ምድር የተቀላቀለበት ሰፈር ነው። «አዲስ አበባ» በተሰኘው ዘፈኑ፡-

**ውብ አዲስ አበባ**
**የትውልድ ሀገሬ**
**ያደኩብሽ መንደር**
**መርካቶ ሰፈሬ**

ሲል ያቀነቀነላት መርካቶ ደግሞ አብዛኛው የልጅነት ሕይወቱን የኖረባት አለሙ ነች። ወደ ሙዚቃ የገባው ቋንቋውን በማያውቀው፣ የስድስት ዓመት ልጅ እያለ በሰማውና «አዝማሪኖ» (ከአስመራ በወጡና አስመራን በናፈቁ ጣልያኖች የተዘፈነ) በተሰኘ ዘፈን በመመሰጥ ነው። ያኔ የዘፈኑ ምንነት ባይገባውም ሙዚቃ የዓለም ቋንቋ መሆኑን አስመስክሯል። እቤታቸው በሚገኘው ሬድዮ ዘወትር አባቱ የሚከፍቷቸውን ሙዚቃዎች በተመስጦ ያጣጥም ነበር፤ በተለይ «አዝማሪኖ» ቋንቋው ባይገባውም ለዘፈኑ የተለየ ፍቅር አደረበት። መጀመሪያ አካባቢ ሥራዬ ብለው ያላስተዋሉት አባቱ የሱ በሙዚቃ መመሰጥ ሲበዛባቸው ልጃቸው አዝማሪ ሲሆን ታያቸው። እሱን ለመከላከል ትልቁን ቴፐ አንስተው ደበቁት። ያኔ ታዲያ ከቤት ወደ ውጪ ሙዚቃን ፍለጋ ውሎውን ቀየረ፤ መርካቶ በሚገኘው ካሊፎርኒያ ሻይ ቤት የሚከፈቱትን ሙዚቃዎች ለማጣጣም ማልዶ መነሳትና ሻይ ቤቱ ደጃፍ ላይ መሰየም የዘወትር ሥራው ሆነ።

ካሊፎርኒያ ደጃፍ የሚሰማቸው ስቲቪ ዎንደር፣ ሀሪ ቤላፎንቴና ሌሎች ጥቁር አሜሪካውያን የተጫወቷቸው የእንግሊዝኛ ዘፈኖች የጉሮሮው ማሟሻ ናቸው። ጥሎበት ለድራም (የሙዚቃ መሣሪያ) ለየት ያለ ፍቅር ነበረው። በዚህ የተነሳ ቆርቆሮ እንደድራም እየመታ ይለማመድ ነበር። ይሄንን ድርጊቱን ያየ፣ ከየመን የመጣ በርካታ የሙዚቃ መሣሪያዎች በቤቱ ያለው ግለሰብ ወደ ቤቱ ወስዶ የሚለማመድበትን ሁኔታ አመቻቸለት። በዚህ የተነሳ ሳይሆን አይቀርም ግሩም ድራም ተጫዋች ነው። ፒያኖ ሲጫወትም ከራሱ አልፎ ሌሎችን የሚያዝናና ሆኗል። ከሻይ ቤት ደጃፍ ዘወትር የሚሰማውን ኤልቪስ ለመሆን ይሞክራል። በየሄደበት ያንጎራጉራል፤ የሱን ሁኔታ ያስመስላል፤ በአፍላነት ዕድሜው የመርካቶው ኤልቪስ ለመሰኘት ጊዜ አልፈጀበትም።

አባቱ ይህ ሁኔታ አልተመቻቸውም። ሁለተኛ ስታዜም ብሰማ ውርድ ከራሴ አሉት። ያኔ ከሙዚቃ ከምለያይ ብሎ ይመስላል ወደ ድሬዳዋ ኮበለለ። ከድሬዳዋ ወደ ሐረር አቀና። በዚያም በምሥራቃዊ ሰጎን ኦርኬስትራ ሙዚቃን መሥራት ጀመረ። አባት በዘመኑ አጠራር የልጃቸው «አዝማሪ» መሆን ሊዋጥላቸው አልቻለም። ከምንም በላይ ደግሞ የእሳቸው ሥም በየመድረኩ መነሳቱ አንገበገባቸው። በዚህ የተነሳም ስሜን እንዳታስጠራ ሲሉ ለልጃቸው ቀጭን ትእዛዝ አስተላለፉ።

ሙዚቃ ከማንም በላይ ናት ያለው ድምጻዊ እሱም የአባቱን ሥም ከጸጋዬ በወቅቱ የፍቅር ጓደኛው በነበረችው አባት ካሳ ቀየረ። «ጌታቸው ጸጋዬ» ከሚለው ሥያሜ ይልቅ የሕይወቱን አብዛኛውን ክፍል «ጌታቸው ካሳ» በሚለው መጠሪያ ተጠርቶበታል። ሐረር እያለ ጥበቡ በላቸው በተሰኘ ሰው የግጥም ደራሲነት «እመኛለሁ» ግጥም ተጻፈ። በጌታቸው የዜማ ደራሲነት እመኛለሁን ይዞ ከአድማጭ ጋር ተገናኘ። ሆኖም የምሥራቅ ቆይታው ማብቃቱን በማመኑ ወደ ትውልድ መንደሩ አዲስ አበባ ተመለሰ። ያኔ የኦርኬስትራው አመራሮች የሱ ከኦርኬስትራው መጉደል የኦርኬስትራው መጉደል መሆኑን በማመናቸው አዲስ አበባ ድረስ አፈላላጊ ልከው በግድ ይዘውት ተመለሱ። ሆኖም «ወታደር ልታደርጉኝ እንደሆነ ስለሰማሁ እዚህ ከዚህ በላይ አልቆይም» ብሎ በመወሰኑ ምንም ማድረግ ሳይችሉ ቀሩ። «እመኛለሁ» ከሕዝብ ጋር ያስተዋወቀው የመጀመሪያ ብሎም ተወዳጅ ሥራው ነው።

**እመኛለሁ**
**እመኛለሁ**
**እመኛለሁ**
**ዘወትር በየለቱ**
**ሳሳካ ኑሮን ከብልሀቱ**
**ኑሮና ብልሀቱ**
**እንስኪቃናልኝ**



ድምጻዊ ጌታቸው ካሳ

**በሃሳብ ግስጋሴ**
**ወደርም የለኝም**
**አልቃና እያለኝ**
**ኑሮና ብልሀቱ**
**መቼውም አልቀረ**
**ምኞት መዘግየቱ**
**አሰብኩት አለምኩት (2 ጊዜ)**
**እኔ ሁሌም**
**አዲስ ነኝ ለዛሬ**

እንዳለውም ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ፤ ውቤ በረሃ ይገኝ በነበረው ፓትሪስ ሉቡምባ ቤት የቤቱ ድምቀት ሆነ። ወዲያው ፈላጊው በዛ እሱን ብለው ሰዎች መጉረፋቸውን ያዩ የምሽት ቤት ባለቤቶች እሱን ለማግኘት ተሻሙ። የአምስት ብር ደሞዙ ወደ አስራ አምስት ብር አድጎ ሰንጋ ተራ አካባቢ ወደ ነበረው ሶንፕሮሬ ክለብ አመራ። ሶንፕሮሬ እየሠራ «ሳይሽ እሳሳለሁ» ለተሰኘ ሥራው ዜማ በመድረስ እውቅናው ይበልጥ ናኘ። እዚያም ብዙ ሳይቆ ወደ አክሱም አዳራሽ ተሸጋገረ።

ጌታቸው ተፈላጊ ገበያ ከፋች ድምጻዊ ነውና ዝውውሩ እንደ ደራ ቀጠለ። ፒያሳ ወደሚገኘው ቬነስ የምሽት ክበብ በማቅናት መሥራት ቀጠለ። እዚያ ሳለ «ምን ይሆን ምስጢሩ» እና «ፍቅርሽን እሻለሁ» የተሰኙ ሙዚቃዎቹን እንካችሁ አለ። በመቀጠልም ወደ ዋቢ ሸበሌ በማቅናት ሙዚቃ መጫወቱን ቀጠለ። በ1964 ዓ.ም የወጣው «ትዝታ» የተሰኘ የትዝታ ሥራው የትዝታ ሥራን ከእንጉርጉሮ አላቆ ለውዝዋዜ ሲጋብዝ የሱም ተወዳጅነት ከፍ አለ። ይሄንን ሥራውን እሱ «እኔ ሳልከፋ ነው» ይላል። ቦብ ዲለን የተሰኘ ዓለማቀፋዊ አርቲስት ምርጥ ስብስቦች መካከል የተካተተ ድንቅ ሥራው ነው።

«ሀገሬን አትንኳት» የተሰኘ ሀገራዊ ሥራው ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ቁርኝቱ ጥብቅ ነው። ነገሩ እንዲህ ነው፤ በ1969 ዓ.ም ሀገር አማን ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ «ኢትዮጵያ ትቅደም!!!» ብሎ በሰላም ሀገሩን ከፊት ለማስቀደም ደፋ ቀና የሚልበት ወቅት ነበር። ያኔ ታዲያ በዚያድ ባሬ የሚመራው የሱማሊያ ጦር ከምሥራቅ አቅጣጫ «ታላቋን ሱማሊያ መፍጠር» በሚል ቅዠት ወረራ ማካሄዱ ተሰማ። በወቅቱ የኢትዮጵያ ሬድዮ ጋዜጠኛ የነበሩት ደራሲ አበራ ለማ በየአቅጣጫው በመዘዋወር ሁነቱን የመዘገብ ዕድል ነበራቸው። ያኔ የጠላት ጦር ወደ ሐረር ከተማ ተቃርቦ የወገን ጦርም ሐረርን ላለማስረከብ የሚከፈለውን መስዋእትነት ታዝበው ወደ አዲስ አበባ ቢመለሱም፤ ሀገሬ ተደፈረች የሚለው ቁጭት ከውስጣቸው አልወጣም ነበር። በዚህ ስሜት ውስጥ ሆነው የጻፉት «ሀገሬን አትንኳት» የተሰኘ ግጥም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ወጣ።

ወቅቱ ድምጻዊ ጌታቸው ካሳ «አሪፍ ግጥም የሚሰጠኝ ሰው ካለ» ብሎ ገጣሚ የሚፈልግበት ወቅት ነበር። ግጥሙን እንደ ብዙሀኑ ኢትዮጵያውያን በጋዜጣው አንብቦ የወደደው ጌታቸው ግጥሙን ለመዝፈን ተነሳስቷል። በዚህ ወቅት ጌታቸውና አበራ ለማን በሚያውቅ፣ ጌታቸው ደገፉ በሚሰኝ ፒያኒስት አማካኝነት ገጣሚውና ዜመኛው ይገናኛሉ። ገጣሚ አበራም በሃሳቡ በመስማማቱ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የወጣው ሀገሬን አትንኳት ተቀንሶና ለዘፈን በሚሆን መልኩ ተስተካክሎ እንዲሠራው ተስማሙ። ያኔ ታዲያ ጌታቸውም ሃሳቡን ስለወደደው 24 ሰዓት ባልሞላው ጊዜ ዜማ ሠራለት። ከደራሲ አበራ «አደሴዋ» የተሰኘ የፍቅር ግጥምም ተቀብሎ ነበርና ሁለቱ ሙዚቃዎች በአንድ ሸክላ ላይ ወጡ። በተለይ «ሀገሬን አትንኳት» ሀገር በጭንቅ ላይ በነበረችበት በዚያ ወቅት የወታደሩን ሞራል ገንቢ ከመሆኑም ባሻገር፤ አሁን ድረስ የሀገር ስሜት ቀስቃሽ፣ ተወዳጅ ዘፈን እንደሆነ አለ።

**ሀገሬን አትንኳት**
**የብዙሀን እናት**
**መጠጊያ የምንላት**
**እማማ ናትና**
**ሀገሬን አትንኳት**
**በዓድዋ በማይጨው**
**ጀግኖች የሞቱላት**
**ሕፃን ሽማግሌ**
**የተሰየፈላት**
**ደመ መራራና**
**ቁጡነት ያለባት**
**ጎጆዬ ናትና**
**ሀገሬን አትንኳት**

የጌታቸውና የሙዚቃ ፍቅር የተለየ ነው። ሙዚቃን ሲል በአፍላነት ዕድሜው ከቤት ኮብልሏል። ዘመዴ፣ ጓደኛዬ ብሎም ሁሉ ነገሬ ለሚላት ሙዚቃ ፍቅር ሲል የአባት ሥም እስከመቀየር የደረሰ መስዋእትነትን ከፍሏል። ያኔ በወጣትነቱ ሒልተን በሳምንት ሰባት ቀን ዘፍኗል። ሰባቱንም ቀን ሙዚቃን ተለማምዷል። በሀገር ቤት ቆይታው ከአማርኛ ሙዚቃዎች በተጨማሪ የእንግሊዝኛ ዘፈኖችንም ይጫወት ነበር። በተለይ ሒልተን ሆቴል ለረዥም ጊዜ የሠራበት ቤት ነው።

በ1981 እ.አ.አ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አሜሪካ በመሄድ ሥራውን ጀመረ፤ በ1986 እ.አ.አ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ። ያኔ ታዲያ ወደ አሜሪካ ከማቅናቱ በፊት ለዘጠኝ አመታት ወደ ሠራበት ሂልተን ተመልሶ ለሁለት ዓመታት ከኢትዮ ስታር ባንድ ጋር ሠርቷል። ቀጣዩን አንድ አመት በግዮን ሲሠራ፤ ሦስቱን ዓመታት አዲስ ያዘጋጀውን አልበም በማጥናት አሳልፏል። ያኔ «አመሰግናለሁ»፣ «እወድሻለሁ»እና ሌሎች ተወዳጅ የሙዚቃ ሥራዎችን የያዘው አልበም ተሠራ። በተለይ አመሰግናለሁ የተሰኘው ተወዳጅ ሥራው አሁን ድረስ የተለያዩ መድረኮች ማጠቃለያ፣ መዝጊያ ሙዚቃ በመሆን እንደተወደደ ዘልቋል።

**አመሰግናለሁ**
**(አንጓዎቹን በመድገም ሁለት ሁለት ጊዜ ነው የሚላቸው)**
**መሄዴ ነው እኔ**
**መሰናበቴ ነው**
**በሉ ደህና ዋሉ**
**አመሰግናለሁ**
**አብረን ባለን ጊዜ**
**ብዙ አሳልፈናል**
**ደጉንም ክፉንም**
**አብረን ተጫውተናል**
**መለየት ቢከብድም**
**ከሚወዱት ሰው**
**አይጠፋም ምንጊዜም**
**አለን ትዝታው**

ስደትን ምርጫው በማድረግ ከ27 ዓመት በላይ መኖሪያውን በአሜሪካ አድርጎ ቢቆይም ዜግነቱን ከመቀየር ይልቅ ተያዝኩ/አልተያዝኩ ብሎ በሰቀቀን መኖርን ምርጫው አድርጓል። በርካቶች ሕይወቱን በቀላሉ እንዲመራ ዜግነት መቀየር ምንም ማለት መሆኑን በመንገር ሊያሳምኑት ቢሞክሩም፣ እሱ ግን «ሀገሬን አትንኳት» ያላትን ሀገሩን መቀየር አሻፈረኝ እንዳለ ኑሮ ባይደላውም ኢትዮጵያዊ እንደሆነ መቆየትን ምርጫው አድርጓል። ያለፉትን አስር ዓመታት መኖሪያውን ሀገር ውስጥ ያደረገ ሲሆን፤ በሀገር ውስጥ በተለያዩ መድረኮችና የምሽት ክበቦች ሙዚቃን ሲጫወት ቆይቷል። ሙዚቃ ከመጫወቱም ባሻገር አብዛኛውን ጊዜ ቤቱ ውስጥ ከፒያኖ ጋር ያሳልፍ ነበር።

50 ዓመታትን በተሻገረው የሙዚቃ ሕይወቱ አምስት አልበሞችን ለአድማጭ አድርሷል። «ብቻዬን ተከዤ»፣ «ትዝታ» ፣ «የኔ አለም»፣ «ብርቱካን ወይ ሎሚ» እና «እንዲህም ናቸው» የሚሉ አልበሞችን ለሕዝብ አድርሷል። «በቁጥር ምን ያህል እንደሆኑ አላውቃቸውም» እስኪል ድረስ የበረከቱ ሙዚቃዎችን ተጫውቷል። በተለይ «ሀገሬን አትንኳት»፣ «ሳይሽ እሳሳለሁ»፣ «እወድሻለሁ»፣ «ትዝታ»፣ «አዲስ አበባ»፣ «ውበትም ይረግፋል» ፣«ትዝ ባለኝ ጊዜ»፣ «የከረመ ፍቅር»፣ «ልውሰድሽ አንድ ቀን»፣ «አትጥፊ ከጎኔ»፣ «አመሰግናለሁ» እና «ቀና ብዬ ባየው» በተሰኙ ተወዳጅ ሙዚቃዎች በደንብ ይታወቃል። ከድምጻዊነቱ ባሻገር በዜማ ደራሲነቱ፣ በድራም እና ፒያኖ ተጫዋችነቱ ይታወሳል። ደግሞም ግሩም መድረክ ተቆጣጣሪም ነበር።

«እንዴት ነህ?» ሲባል በቃል ከማስረዳት በላይ የጄምስ ብራውንን «አይ ፊል ጉድ» በፈገግታ ታጅቦ ማቀንቀን መለያው ነበር። ያለፉትን 79 ዓመታት በዚህ ምድር የኖረው የሙዚቃ መሣሪያ ተጫዋች፣ የዜማ ደራሲ፣ ድምጻዊው የጥበብ ሰው ጌታቸው ካሳ፤ የካቲት 12 ቀን 2016 ዓ.ም ሌሊት በሕክምና ሲረዳ በቆየበት የካቲት 12 ሆስፒታል ሕይወቱ አልፏል። የካቲት 15 ቀን 2016 ዓ.ም በብሔራዊ ትያትር የክብር ሽኝት ተደርጎለት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ወዳጅ፣ አድናቂዎቹና ቤተሰቦቹ በተገኙበት ሥርዓተ ቀብሩ ተፈጽሟል። አዲስ ዘመን ለወዳጅ ዘመዶቹና አድናቂዎቹ መጽናናት ከመመኘቷም በተጨማሪ ድምጻዊ ጌታቸው ካሳ ስለተወልን ዘመን አይሽሬ ሙዚቃዎች «አመሰግናለሁ!!!» ማለት ትወዳለች።

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ በሩሲያ ላይ 500 አዳዲስ ማዕቀቦችን እንደምትጥል አስታወቀች

በጋዜጣው ሪፖርተር

አሜሪካ ሩሲያ በዩክሬን በፈጸመችው ወረራ እንዲሁም በቅርቡ እስር ቤት ሞቶ በተገኘው ተቃዋሚው አሌክሲ ናቫልኒ ጋር በተያያዘ ከ500 በላይ አዳዲስ ማዕቀቦችን እንደምትጥል አስታወቀች።

እነዚህ ማዕቀቦች በሩሲያ ዋነኛ የካርድ የክፍያ ሥርዓት፣ በፋይናንስ እና ወታደራዊ ተቋማት እንዲሁም በናቫልኒ እስራት ውስጥ የተሳተፉ ባለስልጣናት ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ያካትታል ተብሏል።

የአውሮፓ ኅብረት በበኩሉ ከወታደራዊ ቴክኖሎጂ ጋር በተያያዘ አዲስ ማዕቀብ እንደሚጥል አስታውቋል።

ፕሬዚዳንት ፑቲንን በሰላ በመተቸት የሚታወቀው ናቫልኒ በታሰረበት አርክቲክ ሰርክል ከሞተ ከአንድ ሳምንት በኋላም ነው ምዕራባውያኑ አዳዲስ ማዕቀብ እንደሚጥሉ ያስታወቁት።


ሐሙስ ዕለት በሳንፍራንሲስኮ የናቫልኒ ባለቤት እና ልጃቸውን ያገኙት የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ለተቃዋሚው ሞት ተጠያቂው የሩሲያ ፕሬዚዳንት ስለመሆናቸው “ምንም ጥርጥር የለውም” ብለዋል።

አሜሪካ በሩሲያ ላይ የጣለቻቸው አዳዲስ ማዕቀቦች ወደ 100 የሚጠጉ ድርጅቶች እንዲሁም ግለሰቦችን ያጠቃልላል።

የካርድ የክፍያ ሥርዓት የሆኑት ቪዛ እና ማስተርካርድ በሩሲያ አገልግሎታቸውን ማቋረጣቸውን ተከትሎ በሀገሪቱ የካርድ ክፍያ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኘውን ሚር የተሰኘውንም ይህ ማዕቀብ ዒላማ አድርጎታል።

የሩሲያን የጦርነት አቅም በማጎልበት፣ የሀገሪቱን የኃይል ምርት በመደገፍ አስተዋፅኦ ያላቸው እንዲሁም ከኢራን ጋር ድሮኖችን በትብብር የሚሰሩ ኩባንያዎች ማዕቀቡ ይጣልባቸዋል ተብሏል።

ከሩሲያ ውጪም ያሉ በቻይና፣ በተባበሩት አረብ



ጆ ባይደን

ኤምሬትስ፣ በቬትናም እና በሊችተንስታይን ያሉ ግለሰቦች እና ተቋማት ቁሳቁሶችን ወደ ሩሲያ ጦር ከሚልኩ የንግድ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል የማዕቀቡ ኢላማ ተደርገዋል።

ማዕቀቡ በሩሲያ ምጣኔ ሀብት ላይ ይህ ነው የሚባል ተፅዕኖ ይኖረዋል ተብሎ አይታሰብም። ሩሲያ ቀድሞውኑ በምዕራባውያኑ ከፍተኛ ማዕቀብ የተጣለባት ሀገር ስትሆን በአሜሪካ እና በአውሮፓ እገዳ ያልተደረገባቸው የንግድ ዘርፎች በጣም ጥቂት ናቸው።

የሩሲያ ባንኮች እና ወታደራዊ ኢንተርፕራይዞች ማዕቀቦቹን ለማምለጥ የተለያዩ መንገዶችንም አዘጋጅተዋል ተብሏል።

የዩክሬን ባለስልጣናት በቁጥጥር ስር ባዋሏቸው የሩስያ ሰው አልባ አውሮፕላኖች (ድሮኖች) ውስጥ የአሜሪካ እና የአውሮፓ ስሪት የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ማግኘታቸውን ገልጸው፤ ዝርዝሩን ይፋ አድርገዋል። አብዛኛዎቹ እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ከቻይና በኩል ወደ ሩሲያ የሚላኩ ናቸውም ተብሏል።

## የሴኔጋሉ ፕሬዚዳንት በመጋቢት ወር መጨረሻ ሥልጣናቸውን ለመልቀቅ ተስማሙ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የሴኔጋሉ ፕሬዚዳንት ማኪ ሳል የሥልጣን ጊዜያቸው መጋቢት 24 ቀን 2016 ዓ.ም ሲያበቃ ሥልጣናቸውን እንደሚለቁ አስታወቁ።

ሆኖም ምርጫ የሚካሄድበት ቀን ባለመቆረጡ በሀገሪቷ ውስጥ ውጥረት ተከስቷል።

ፕሬዚዳንቱ እሑድ ዕለት ይካሄዳል ተብሎ ታቅዶ የነበረውን የምርጫ ጊዜ ወደ መጪው ታህሳስ ወር መጀመሪያ ማራዘማቸው የበርካቶችን ሕይወት የቀጠፈ ተቃውሞ አስከትሏል።

ሳል በቴሌቪዥን በተላለፈ ቃለ ምልልሳቸው ላይ የምርጫው ቀን በመጪው ሰኞ በሚካሄደው ፖለቲካው ንግግሮች እንደሚወሰን ተናግረዋል።

ሆኖም ተቃዋሚዎች በንግግሩ ላይ ለመሳተፍ ፈቃደኛ አልሆኑም። ይህም ውጥረቱን ያረግባል ተብሎ የተጣለውን ተስፋ አጨልሞታል።

ከ19ኙ ፕሬዚዳንታዊ እጩዎች መካከል 16ቱ፣ ፕሬዚዳንቱ “ብሔራዊ ምክክር” ሲሉ በጠሩት ውይይት ላይ እንደማይሳተፉ የገለጹ ሲሆን፤ በርካታ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችም ለመሳተፍ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል።

በናይጄሪያ፣ አቡጃ ለሚካሄደው የምዕራብ አፍሪካ ሀገራት የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ (ኢኮዋስ) ስብሰባ ያቀኑት ሳል፣ ባለፈው ሳምንት የሰኔጋል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ምርጫውን ማራዘም ሕገ ወጥ ነው ካለ በኋላ ምርጫው የሚካሄድበትን ቀን እንዲቆርጡ ግፊት እየተደረገባቸው ነው።

ፕሬዚዳንቱ ቀደም ብሎ የምርጫውን ጊዜ ለማራዘም ያሳለፉት ውሳኔም ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብም ተቃውሞ ገጥሞታል።

በርካቶች የምርጫው ጊዜ መራዘሙ በመፈንቅለ መንግሥት እና በወታደራዊ መንግሥታት በሚናጠው ቀጣና ሳልን ላልተወሰነ ጊዜ መሪ ሆነው እንዲቀጥሉ ያደርጋል ሲሉ ስጋታቸውን ገልጸዋል።

ሳል ሐሙስ ምሽት በቴሌቪዥን ባስተላለፉት ንግግር፤ እርሳቸው መጋቢት ወር መጨረሻ ላይ ሥልጣናቸውን



ፕሬዚዳንት ማኪ ሳል

እስከሚለቁ የሚተካቸውን ሰው ለመምረጥ በቂ ጊዜ የለም ብለው እንደሚያምኑ ተናግረዋል።

በመሆኑም ምን መሆን እንዳለበት ምክክሩ ይወስናል ብለዋል።

ፕሬዚዳንቱ በንግግራቸው ታዋቂውን የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ ኦስማን ሶንኮን ከእስር ለመፍታት መዘጋጀታቸውንም ገልጸዋል።

ሶንኮ ለክስ እና ለእስር የተዳረገው በቀጣዩ ምርጫ ተገዳዳሪ በመሆን ለገዢው ፓርቲ ስጋት እንዳይሆን ለማድረግ ነው ሲሉ ተቃዋሚዎች ይከሳሉ።

የፖለቲከኛው እስር ባለፈው ዓመት በመላ ሀገሪቷ ተቃውሞ ቀስቅሶ ነበር።

የሴኔጋል የሕገ መንግሥት ምክር ቤት የምርጫ ጊዜውን ማራዘም ሕገ ወጥ ነው ካላ በኋላ በርካታ የፕሬዚዳንቱ ተቃዋሚዎች ከእስር ተለቀዋል።

ሆኖም ፕሬዚዳንቱ ምርጫ የሚካሄድበትን ቀን ባለመቁረጣቸው በስልጣን ለመቆየት የሚያደርጉት ስልት ነው በሚል በተቺዎቻቸው ዘንድ ጥርጣሬን ፈጥሯል።

ፕሬዚዳንት ሳል ለሁለት የሥልጣን ዘመን ሀገሪቷን የመሩ ሲሆን፤ እንደ አውሮፓውያኑ በ2012 ለመጀመሪያ ጊዜ ፕሬዚዳንት ሆነው ሲመረጡ ከተሰጣቸው ጊዜ በላይ በሥልጣን መቆየት እንደማይፈልጉ ቃል ገብተው ነበር።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቀምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ያልገባን የዓድዋ. . .

ከ ገጽ 3 የዞረ

ማዶ ተፋጠጠ። የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም በተካሄደ ጦርነት የጀኔራል ባራቲየርና የሌሎች ጄኔራሎች ጦር ተሸነፈ። ሸሸ። ተፈታ። ወደ 10ሺህ የሚጠጋ የጣሊያን ጦር ሙት፣ ቁስለኛ፣ ምርኮኛ መሆኑን አንዳንድ የታሪክ ድርሳናት ሲያትቱ ፤ ሌሎች ደግሞ የሟቹን ቁጥር 11ሺህ ፣ የተማረከውን 4ሺህ ያደርሱታል ።

ከጄኔራሎች አርሞንዲና ዳቦርሚዳ ሲሞቱ ፤ በ1850ዎቹ የሀገራቸውን ነፃነትና አንድነት በማስከበሩ ብሔራዊ ጀግና ከነበረው ጁሴፔ ጋሪባልዲ ጋር ይነፃፀር የነበረው የጄኔራል አርቤርቶኔ መማረክ ለጣሊያናውያን ሌላው አስደንጋጭና በሀፍረት አንገት ያስደፋ መርዶ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ። ከጦር መሣሪያም መድፍ ፣ 11ሺህ ጠመንጃ ፣ በርከት ያለ ጥይትና ቁሳቁስ ተማርኳል። ከኢትዮጵያ የጦር አበጋዞችና የንጉሡ የቅርብ ባለሟሎች ጀግናውን ፊታውራሪ ገበየሁ፣ ልዑል ዳምጠው፣ ደጃዝማች መሸሻ፣ ደጃዝማች ጫጫ፣ ቀኛዝማች ገነሜና ሌሎች ለሀገራቸው ነፃነትና ሉዓላዊነት መውደቃቸውን፤ በተጨማሪም 4ሺህ ሲሞቱ 6ሺህ ኢትዮጵያውያን መቁሰላቸውን የተለያዩ የታሪክ ሰነዶች ቢያትቱም ቁጥሩ ከዚህ ሊበልጥ እንደሚችል ይገመታል።

ዘመናዊ የጦር መሣሪያ እስከአፍንጫው የታጠቀው የጣሊያን ጦር አፍሪካዊና ኋላቀር በሆነ የገበሬ ጦር የኢትዮጵያ ሕዝብ መረታቱ ለማመን የሚቸግር መነጋገሪያ ሆነ። አንዳንድ ምዕራባውያን ፖለቲከኞችና ሚዲያዎች የኢትዮጵያውያንን ጥቁርነት እስከ መካድ ደርሰው ነበር። የታላቁ የዓድዋ ድል የአፄ ምኒልክንና የእቴጌ ጣይቱ (ብርሃነ ዘኢትዮጵያ) ዝና በመላው ዓለም እንዲናኝ ከማድረጉ ባሻገር ሀገሪቱን በዓለምአቀፉ የዲፕሎማሲ መድረክ መነጋገሪያ አደረጋት።

ከአፅናፍ አፅናፍ የዓለምን ትኩረት እንድትሰብ አደረጋት። ድሉ ጥቁሮች ነጮችን ድል መንሳት እንደሚችሉ በማሳየቱ ፤ በቅኝ ግዛት፣ በጭቆና ለሚገኙ የዓለም ሕዝቦች በተለይ ለአሜሪካ ጥቁሮች መነቃቃትን ፈጥሯል። ለማርከስ ጋርቬ ፣ ለፓን አፍሪካኒዝም ፣ ለኔልሰን ማንዴላ ፣ ለኩዋሚ ንኩሩማህ፣ ለስቲቭ ቢኮ እና ሌሎች ንቅናቄዎች እርሾ በመሆን አገልግሏል፡፡ ለደቡብ አፍሪካ የፀረ አፓርታይድም ሆነ ለሌሎች ለፀረ ቅኝ ግዛት ትግሎች ጉልበት ሆኖ አገልግሏል። የአረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲራችን ከ20 በላይ የአፍሪካና የካሪቢያን ሀገራት ሰንደቅ በተለያየ ቅርፅ የመገኘቱ ምስጢርም ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው። የግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ አህጉራዊና ዓለምአቀፋዊ ተቀባይነትም የራሳቸው ጥረት እንዳለ ሆኖ መነሻው አንፀባራቂው የዓድዋ ድል ስለመሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ። አንዳንድ የፖለቲካና የታሪክ ልሂቃን የትናንቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (አአድ) ሆነ የዛሬው የአፍሪካ ኅብረት (አ ህ) የምስረታ ሃሳብ የዓድዋ መንፈስ የበኩር ልጅ የሆነው የፓን አፍሪካኒዝም የመንፈስ ክፋይ ነው ይሉታል።

### የዓድዋ ትምህርት

በዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህር የሆነው ሬይሞንድ ጆናስ የዓድዋን ድል ትምህርት ፣ አንድምታ፣ ጥልቀት ፣ ከፍታ ፣ ንዑድነትና ትርጉም በሚያስደንቅ ሁኔታ እንዲህ ይገልፀዋል ፡- «...ምኒልክ እና ጣይቱ ወደ ሰሜን የዘመቱት ሥልጣናቸውን በፅኑ መሠረት ላይ ለመገንባት ብቻ አልነበረም ። ... የትግራይ ፣ የሸዋ ፣ የኦሮሞ ፣ የወላይታ እና የሌሎች ሕዝቦችን ውስጣዊ አንድነት በደም አስተሳስረው በጋራ ጠላት ላይ በመዝመት የጋራ ሀገር ለመገንባት እንጂ፤ የሕዝቦች ጥብቅ ትስስር የሚፈጠረው በእያንዳንዱ ሃይማኖት ፣ ማንነት ብሔር ላይ ተመስርቶ ሳይሆን የጋራ ነፃነትን ለመቀዳጀት በሚከፈል መስዋዕትነት ነው።

ይህ ዓይነቱ መተሳሰር ብቻ ነው የኢትዮጵያ የነፃነት ከፍታ መገለጫ፤ የዓድዋ ትምህርትም ይኸው ነው። ልንታደለው የሚገባን ነፃነት ልንከላከለው የሚገባ መሆን እንዳለበት ዓድዋ ያስታውሰናል። የዓድዋ ድል ያስገኘው ነፃነት ብቻ ሳይሆን የተገኘበትን መንገድ ብናጤነው የዘመናችንም ታላቅ ወታደራዊ ድል እንድሆነ እንረዳለን። በጠመንጃ ብቻ በመታገዝ የተገኘ ድል አይደለም። የበርካቶችን ልብ በማሸነፍ እንጂ ፤ ...»

ይህ የሬይሞንድ ጥልቅ ፣ ምጡቅ የዓድዋ ትምህርት፣ ፍልስፍና ዳጎስ ዳጎስ ያሉ መፅሐፍት የሚወጣው ከመሆኑ ባሻገር አዲስ አተያይን ንጻሬን የገላለጠ ነው ማለት ይቻላል። የዓድዋን ትምህርት ሀገራችንና ሕዝባችን ከሚገኙበት ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሊተረጎም ፣ ሊተነተን ፣ ሊመከርበት የሚገባ ከቡድ ሃሳብ ነው። በአንድ በኩል የምንገኝበትን ዘመንና ትውልድ የዋጀ፤ ከፍ ሲልም እኛን እንደ ዜጋ ተከሳሽ ሳጥን ላይ አቁሞ በመስቀለኛ ጥያቄዎች የሚሞግት፣ የሚዳኝ ሆኖ ይሰማኛል። በሌላ በኩል በአግባቡ ተንትነን ከተረዳነው መሻገሪያ ይሆነናል።

አዎ ! በጀግኖች አባቶቻችን ከ124 ዓመታት በፊት የተቀዳጀነውን ታላቁ የዓድዋ ድልም ሆነ፤ ከጣሊያን የአምስት ዓመቱ ቆይታ፤ ከንጉሣዊ አገዛዙ፤ ከጊዜአዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ነፃ የወጣንባቸውን ድሎች ልንከላከላቸውና ልንጠብቃቸው ባለመቻላችን ለአንድ ምዕተ ዓመት ከሩብ ለዘለቀ አሳር እንደዳረገን ውድ ዋጋ እንዳስከፈሉን በጥሞና ልናንሰላስለው ይገባል። የሚያሳዝነው ከእነዚህ ወሳኝ የታሪክ መታጠፊያዎች ዛሬም አለመማራችን ነው። ብልጥ ብንሆን ከሌሎች የሰው ልጆች ታሪክ መማር በቻልን።

እኛ ግን ከራሳችን ታሪክ መማር ባለመቻላችን ዛሬ ለምንገኝበት ቅርቃር ዳርጎናል። ከትናንቱ የ27 ዓመታት ግፍ ፣ መከራና አሳር እንኳ መማር አልቻልንም። አይደለም የዓድዋውን፣ የአምስት ዓመት የጣሊያን ወረራ ፣ የደርግና የትህነግ / ኢህአዴግ ነፃነቶችን ባለፉት አምስት አመት በአደራ የተረከብነውን የነፃነት ቀብድ እንደቀደሙት ባክኖ፣ ትርጉም አጥቶ እንዳይቀር በአግባቡ ለመጠቀም፣ ከቅልበሳ ለመከላከልና ለመጠበቅ የተዘጋጀን አይመስልም።

ሬይሞንድ ከላይ አፄ ምኒልክ ፣ እቴጌ ጣይቱ ወደ ሰሜን የዘመቱት ወራሪውን ፋሽስት ጣሊያን ድል ለመንሳት ብቻ አልነበረም። የሀገሪቱን ውስጣዊ አንድነት በደም አስተሳስረው በጋራ ጠላት ላይ በመዝመት የጋራ ሀገር ለመገንባት እንጂ ይለናል። ይሁንና ዛሬ ሀገራችን ድንበርን ተሻግሮ የሚወር ጠላት ባይኖራትም ከታላቁ የሕዳሴ ግድብ ጋር ተያይዞም ሆነ በሌሎች ፈተናዎች በብሔራዊ ጥቅሟ ጉሮሮ ላይ ለመቆም የጦር ዕቃውን ታጥቆ፣ የራስ ቁሩን ደፍቶ፣ ጡሩሩን ለብሶ፣ ጦሩን እየሰበቀና ዘገሩን እየነቀነቀ ግዳይ ለመጣል አጋጣሚውን በንቃት የሚጠብቅ ኃይል መኖሩን ልብ ያልን አይመስልም። በቅጡ ተረድተናቸዋል የሚል እምነት ግን የለኝም። ለሥልጣን ጥም ማርኪያ ብሔራዊ ጥቅሟን ፣ ሀገራዊ አንድነቷን ያለምንም ማቅማማት አሳልፎ ለመስጠት በጥፍሩ የቆመ ኃይል መኖሩን አናንቀነዋል።

የሰላማችን፣ የአንድነታችን፣ የሉዓላዊነታችንና የተስፋችን ስጋት የሆኑ ኃይሎችን ልናስቆማቸው የምንችለው አያት ቅድመ አያቶቻችን የዓድዋ ድል ለመቀናጀት በአንድነት እንደቆሙት ሁሉ እኛም ልዩነቶቻችንን አቆይተን ይሄን ክፉ ቀን ለማለፍ ዳር እስከ ዳር እጅ ለእጅ ተያይዘን በአንድነት መቆም ስንችል ነው። በታላቅ መስዋዕትነት እጃችን የገባ የጋራ ነፃነትን ለመከላከልና ለመጠበቅ ሌት ተቀን በንቃት መቆም አለብን። የዓድዋ አንጸባራቂ ድል የተመዘገበው ሰው ተከፍሎለት አጥንት ተከስክሶለት፣ ደም እንደጎርፍ ፈሶለት እንጂ ዳር ቆሞ አይዞህ በማለት አይደለም።

በሀገራችን ሀቀኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአለት ላይ እንዲመሠረት መተኪያ የሌላት የሀገራችን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር ጣት መጠቋቆሙን፣ መጠላለፉን ፣ ልዩነትን፣ ወንዜነትን፣ አቃቂር ማውጣቱን፣ አቅላይነትን ፣ አሉባልታውን ፣ ወዘተ. ትተን የመፍትሔው አካል በመሆን የዜግነት ግዴታን መወጣት ይጠይቃል። የዓድዋ ትምህርት ሀ ሁ .... ይህ ነው። ለአለፉት 127 ዓመታት ብንቆጥረው ብንቆጥረው አልገባን፣ አልገባው ያለን የታሪክ ፊደል።

ለእነ ማዲባ ፣ አሊቨር፣ ንኩሩማህ ፣ ማርከስ ፣ ስቲቭ ቢኮ፣ ጆሞ፣ ሙጋቤ፣ ቦብ፣ ለመላው አፍሪካ ፣ ለዩናይትድ ስቴትስ ሙብት ተሟጋቾች ለእነ ማርቲን፣ ሮዛ ፣ ጄሲ ጃክሰን፣ ማልኮም ኤክስ ፣ ሉዊስ ፋራካህ፣ ኤሊጃህ ሞሀመድ፣ አባማ የተቆጠረው የፊደል ገበታ እኛ በአጥንት፣ በማንነት ፖለቲካ፣ በታሪክ ምርኮኝነት፣ በታሪክ ሽሚያ ተጋርዶብን፣ ዛሬም ቅኔ፣ ምስጢር እንደሆነ አለ። በዚህ የተነሳ የጋራ ህልም፣ ርዕይ፣ የታሪክ ብያኔ ፣ የጋራ ጀግና፣ የጋራ ድል፣ የጋራ ሀገር፣ የጋራ መሪ፣ የጋራ መነሻና መዳረሻ ፣ ...፤ እንዳይኖረን አድርጓል ።

ግርዶሹን ለማንሳትና ከሚያለያዩን ይልቅ አንድ የሚያደርጉንን ማንነቶችን መመልከት እንድንችል በአያት ቅድመ አያቶቻችን ሰው የመሆን ኢትዮጵያዊ ንስር ዓይን እንመልከት። እንኳን ታላቁ የሰው ልጆች ሁሉ የነፃነት የድል በዓል የሆነው ዓድዋ 127ኛ አመት ደረሰባችሁ። ደረሰብን። እኛ እዚያ ከፍታ ላይ መድረስ አይደለም ከማንነት ፌርማታችን ገና አልተንቀሳቀስንም።

ሻሎም ! አሜን።

**የንጉሡ ጦር በወርሐ የካቲት እኩሌታ ለዓድዋ ጥቃት ዝግጁ ሆነ። የጣሊያንና የኢትዮጵያ ጦር ወዲና ማዶ ተፋጠጠ። የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም በተካሄደ ጦርነት የጀኔራል ባራቲየርና የሌሎች ጄኔራሎች ጦር ተሸነፈ። ሸሸ። ተፈታ። ወደ 10ሺህ የሚጠጋ የጣሊያን ጦር ሙት፣ ቁስለኛ፣ ምርኮኛ መሆኑን አንዳንድ የታሪክ ድርሳናት ሲያትቱ ፤ ሌሎች ደግሞ የሟቹን ቁጥር 11ሺህ ፣ የተማረከውን 4ሺህ ያደርሱታል**

# ስፖርት



## ጄሲ ኦውንስ- ጥቁሮችን ያስከበረ ኮከብ

**ቦጋስ አበበ**

የካቲት ወር ለኢትዮጵያውያን ልዩ ወር ነው። ከዓድዋ እስከ ካራማራ ታሪካዊ ድሎች በዚሁ ወር የተከሰቱ ናቸው። ኢትዮጵያውያን የመላውን ዓለም ጥቁር ሕዝቦች አንገት ቀና ያደረጉበትን የዓድዋ ድልን የሚያከብሩበት ወርሀ የካቲት በመላው ዓለምም የጥቁር ሕዝቦች ወር ሆኖ ይከበራል። በሰሜን አሜሪካ፤ ካናዳና ሌሎች ሀገራት በየዓመቱ ከሚከበረው የጥቁር ሕዝቦች የታሪክ ወር ሲዘከር በስፖርቱ ዓለምም ከጥቁር ሕዝብ የፈለቁ ጀግኖች ይታወሳሉ።

ጥቁር ስፖርተኞች በዘመናችን በዓለም ታላላቅ ውድድሮች የገዘፈ ተፅእኖ ቢኖራቸውም እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረሳቸው አያሌ ጥቁር ከዋክብት በቆዳ ቀለማቸው መጥቆር ተንቀዋል፣ አይችሉም ተብለው ተገፍተዋል፣ እኩልነታቸውን ለማንፀባረቅም ብዙ መስዋእትነት ከፍለዋል።

በአትሌቲክስ አበበ ቢቂላ፣ በእግር ኳስ ፔሌ፤ በቦክስ መሐመድ አሊን የመሳሰሉ ከዋክብት በዓለም ገናና የስፖርት መድረኮች የጥቁር ስፖርተኞችን እኩልነት ማሳየት የቻሉ ፋና ወጊዎች ናቸው።

የጥቁር ሕዝቦች ወርን ከዚያም የዓድዋ ድልን ስናከብር በስፖርት ውስጥ ለጥቁር ሕዝቦች ተምሳሌት ለመሆን ከበቁ ኮከቦች አንዱ የሆነውን ጄሲ ኦውንስን በዛሬው የስፖርት ማህደር አምዳችን መለስ ብለን እናስታውስ።

1913 በአላባማ የተወለደው ጄሲ ትክክለኛ ስሙ ጄምስ ክሊቭላንድ አውንስ ሲሆን በልጅነቱ “JC” 



**ጄሲ ኦውንስ ለበርካታ ጥቁር ስፖርተኞች አርአያ ነው፤**

ተብሎ ይጠራ ነበር። ወደ ኦሃዮ ከመጣ ወዲህ ግን መምህሩ ስሙን “እሴይ” ሲል ተሳስቶ በዚህ ስም ታወቀ።

ጄሲ አትሌቲክስን የጀመረው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ሲከታተል በነበረበት ወቅት ነው። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባደረገው የመጀመሪያ ውድድር የዓለም ክብረወሰን ካስመዘገበ በኋላም ወደ ኦሃዮ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ገባ። በአትሌቲክሱም ትልቅ ስኬት ማስመዝገቡን ቀጠለ።

እኤአ በ1935 በሚቺጋን በተካሄደው ቢግ 10 በተሰኘ ቻምፒዮና ጄሲ በ45 ደቂቃ ውስጥ አራት የዓለም ክብረ ወሰኖችን ሰበረ። እነዚህም 100 ያርድ (9.4 ሰከንድ)፣ ረጅም ዝላይ (8.13 ሜትር)፣ 220 ያርድ (20.3 ሰከንድ) እና 220 ያርድ መሰናክሎች (22.6 ሰከንድ) ነበሩ። ይህም አስደናቂ ብቃቱ አሜሪካን በኦሊምፒክ ለመወከል አበቃው።

ጊዜው እኤአ 1936 ነው፣ ውድድሩ ደግሞ ታላቁ ኦሊምፒክ። ወቅቱ የኦሊምፒኩ አዘጋጅ የሆነችው ጀርመን ብቻ ሳትሆን አብዛኛው የዓለም ሀገራት በናዚ ሥርዓት አራማጁ አዶልፍ ሂትለር የብረት መዳፍ የሚታሹበት ነበር።

ጄሲ አሜሪካንን ወክሎ በሂትለር ገዢነት በናዚ የተዘጋጀው የበርሊን ኦሊምፒክ ከመሄዱ በፊት በአሜሪካ የሚደርሰውን የሰብአዊ መብት ጥሰት እንዲሁም ሂትለር የሚፈጸመውን የሰብአዊ መብት ጥሰት የሚቃወሙ ኃይሎች የአፍሪካን አሜሪካውያን አክቲቪስቶች ውድድሩን እንዳይሳተፍ ይወሰውሱት ነበር። እናም አንድ ቀን ለነጭ አሰልጣኙ ወደ በርሊን ለመሄድ ማመንታቱን ተናግሮ ነበር።

ኦሊምፒኩ በአዶልፍ ሂትለር ናዚ ጀርመን ሲካሄድ “የላቀ የጀርመን ዘር” ወይም የአርያን ሕዝብ የበላይነት ማሳያ እንዲሆን የታቀደ ዝግጅት ነበር።

ሆኖም ጥቁሩ አሜሪካዊ አትሌት ጄሲ አውንስ በአስደናቂ ድሎቹ እነዚህን እቅዶች በማክሸፍ በኦሊምፒኩ አራት የወርቅ ሜዳሊያዎችን አጥልቆ ናዚዎች የሚተናነቁትን ድል ማጣጣም ችሏል። እነዚህ የወርቅ ሜዳሊያዎች፡- በ100 ሜትር (10.3 ሰከንድ)፣ በ200 ሜትር (20.7 ሰከንድ)፣ በርዝመት ዝላይ (8.06 ሜትር) እና 4×100 ሜትር ዱላ ቅብብል (39.8 ሰከንድ) ያስመዘገባቸው ነበሩ።

በእነዚህ ስኬቶች ጄሲ አውንስ የጥቁር ሕዝቦች እና የአሜሪካውያን ኩራት ሆነ። አሜሪካ በዚያ ኦሊምፒክ ካገኘቻቸው 11 ሜዳሊያዎች ስድስቱ በጥቁር አፍሮ አሜሪካዊያን አትሌቶች፣ በተለይም አራቱ የወርቅ ሜዳሊያዎች በጄሲ አውንስ የተገኙ ናቸው፡፡

የድሉ ሜዳሊያ መሰጠት ሲጀመርም አንድ ልብን የሚነካ ነገር ይሆናል፡፡ በዘረኝነት ልቡ የደነደነው አዶልፍ ሂትለር ስቴዲየሙን ለቆ ወጣ፡፡ የጥቁር ሰው እጅ አልጨብጥም፣ የድሉን ሜዳሊያም ከጥቁር ሰው አንገት አላጠልቅም ነበር ምክንያቱ፡፡

ጄሲ ከታሪካዊ ድሉ በኋላም ወደ ሀገሩ አሜሪካ ሲመለስ በኋይት ሃውስ አቀባበል ቢደረግለትም የወቅቱ ፕሬዚዳንት ሮዝቤልት እንደ ሂትለር ሁሉ ሊጨብጡት እጃቸውን አልዘረጉለትም። ከኦሊምፒክ ድሉ መልስ ሌላው ቢቀር ዝነኝነቱ እንኳን ሥራ አላስገኘለትም። ነዳጅ ማደያ ውስጥ ሥራ ያገኘው ከብዙ ውጣ ውረዶች በኋላ ነው። የእንዲህ አይነቱ አበሳ መብዛት ምክንያቱ ዘረኝነት በአሜሪካ ምድር ያለ ቅጥ መስፋፋቱ ነበር።

አፍሪካ አሜሪካዊው አውንስ ከ32 ዓመቱ ጀምሮ ለ35 ዓመታት ያህል ሲጋራ ያለማቋረጥ አጭሷል። ይህም በደረሰበት በደል የብስጭቱ ውጤት እንደነበር የቅርብ ወዳጆቹ ተናግረዋል። ይህ ግን የጎዳው ራሱን ነበርና በመጨረሻም በሳንባ ካንሰር ሲሰቃይ ቆይቶ እኤአ በ1980 ይህችን ዓለም ተሰናብቷል። ከዓመታት በኋላም የጀግና ሃውልት ቆሞለታል።

ጄሲ እንደ ሠራው ታሪክ የሚመጥነውን ህይወት ሳይኖር ቢሞትም በስፖርቱ ዓለም የሠራው ታሪክ ህያው ሆኖ ዛሬም ድረስ ይወደሳል።




# የአንጋፋዎቹ ምክር ለልጆች

**እየሩስ ተስፋዬ**

ሰላም ልጆችዬ እንዴት ናችሁልን? ትምህርት፣ ጥናት እንዴት ነው? እየበረታችሁልን ነው? ጎበዞች በርቱ እሺ። ልጆችዬ፣ እናንተ ነገ ጥሩ ሰው እንድትሆኑ፤ እንዲሁም በትምህርታችሁ ጥሩ ውጤት እንድታስመዘግቡ እና ሀገራችሁን የምታኮሩ ዜጎች እንድትሆኑ ሁሉም ሰው መልካሙን ሁሉ እንደሚመኝላችሁ ትገነዘባላችሁ ብለን እናስባለን። መመኘት ብቻ አይደለም፤ ስትጎብዙ ‹‹ቀጥሉበት›› ስታጠፉ እና ስትሰንፉ ደግሞ ከስህተታችሁ እንድትማሩ የሚመክሯችሁ እና የሚቆጧችሁ ለእናንተ ብለው እንደሆነ ታውቃላችሁ አይደል ልጆች? በጣም ጥሩ።

ስለዚህም ልጆችዬ ከዚህ ቀደም ልጆችን በተመለከተ በተካሄደ አንድ መድረክ ላይ ለእናንተ መልካም ምኞታቸውን እና ምክራቸውን ካስተላለፉ አንጋፋ እና ታዋቂ ሰዎች መካከል ውስጥ ያስተላለፉላችሁን መልዕክት እናቀርብላችኋለን። በተጨማሪም ስለ እነርሱ በጥቂቱ እንነግራችኋለን።

ልጆችዬ፣ የክብር ዶክተር ዳዊት ይፍሩን ታውቋችኋላችሁ? ለማታውቋቸው እንግዲያውስ እናስተዋውቃችሁ። በኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ ትልቅ ዐሻራ የጣሉ ናቸው። የሙዚቃ ባለሞያው የክብር ዶክተር ዳዊት በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ የሙዚቀኞች ማኅበርን በፕሬዚዳንትነት እየመሩ ይገኛሉ። የእርሳቸው ምክርም፡-

«በተለያዩ መድረኮች ላይ ጥሩ ሥራ በመሥራት የሚሸለሙ ልጆች አሉ አይደል? ስለዚህም ልጆች እንደ እነርሱ ጎበዝ መሆን አለባችሁ።»

የሚል ነው። ለወደፊት የምትመኙት እና መሆን የምትፈልጉት ደረጃ ላይ ለመድረስም ከፍተኛ ጥረት እና ከፍተኛ የሆነ ልምምድ እንደሚያስፈልግ ነው የተናገሩት።



**ሲስተር ዘቢዳር ዘውዴ**



**የክብር ዶክተር ዳዊት ይፍሩ**

‹‹የምትፈልጉትን ነገር ለማግኘት ጥረት እና ብዙ መሥራት እንዳለባችሁ እንድትገነዘቡ አደራ እላለሁ፡›› ሲሉም ነው ለእናንተ መልካሙን ምክራቸውን የለገሱት።

አርቲስት፣ መምህር እና ሠዓሊ ጋሽ አክሊሉ መንግሥቱ ብዙዎች አርቲስት እና ሠዓሊ በሚለው ስያሜ ያውቋቸዋል። እርሳቸው እንደሚናገሩት ልጆች ዓይናቸው ሁልጊዜ ንጹህ ነው። ሁሌም ንጹህ ሆነው በጥሩ መንገድ እንዲያድጉ ወላጆች በአግባቡ ማሳደግ፣ መንከባከብ እና ትልቅ ቦታ እንዲደርሱ ማድረግ ላይ ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው።

ልጆችዬ፣ ጥሩ መልዕክት ነው አይደል? ታዲያ እናንተም ጥሩ ልጅ ለመሆን ወላጆች የሚሏችሁን እንደምታዳምጡ ምንም ጥርጥር የለኝም።

ወደ ጠንካራዋ ሴት እንለፍ አይደል? ሲስተር ዘቢደር ዘውዴ «የሜሪጆይ ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት» መሥራች ናቸው። በበጎ አድራጎት ሥራቸው ይታወቃሉ። ሴቶችን፣ አረጋውያን እና ሕፃናትን በመርዳት ከ20 ዓመት በላይ ተሻግረዋል። እርሳቸውም ለእናንተ ጥሩ መልዕክት አላቸው።

ሲስተር ዘቢደር በመጀመሪያ ደረጃ ልጆች ፈጣሪን መፍራት እንዳለባቸው ነው የሚመክሩት። ሁለተኛው ምክራቸው እናት እና አባቶቻችሁን (አሳዳጊዎቻችሁን) እንድታከብሩ በጣም አደራ ብለዋል። ሦስተኛው ምክራቸው ደግሞ ምን መሰላችሁ፣ ጎዳና ላይ ብዙ ሕፃናት ታያላችሁ አይደል? በጣም የተቸገሩ እናቶች፣ ትምህርት ቤት መሄድ የማይችሉ ታዳጊዎች፣ ሕክምና የማያገኙ በጣም የሚያሳዝኑ ልጆች ስላሉ፤ ለእነርሱ ልብስ በመስጠት እና የተለያዩ ድጋፎችን እንድታደርጉላቸው፤ እንዲሁም የተቸገረን ሰው መርዳት እንዳለባችሁ የሚያሳስብ ነው። ‹‹ይህንን በማድረጋችሁ ፈጣሪን ታስደስታላችሁ።›› ሲሉም መልካሙ ምክራቸውን እንካችሁ ብለዋል።

ደራሲ እና ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠም መልዕክት አላቸው። ‹‹ልጆች ስለ ሀገራቸው ጠንቅቀው እንዲያውቁ በታሪክ ዙሪያ የሚጻፉ መጽሐፍትን ማንበብ ይኖርባቸዋል። ስለሀገራቸው ያላቸው ግንዛቤ ከፍ ማለት ይኖርበታል።›› በማለት ልጆች ላይ ብዙ ነገር መሥራት እንደሚገባም ጥቆማ አድርገዋል።

ልጆችዬ አንጋፋ አርቲስቶች፣ እንዲሁም በጎ አድራጊ ሰዎች እናንተ ትልቅ ቦታ እንድትደርሱ በመመኘት እና ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ያስተላለፉላችሁን ምክር ወደዳችሁት አይደል? ‹‹በሚገባ ወደነዋል።›› የሚል መልስ እንደሰጣችሁኝ ምንም ጥርጥር የለኝም። መውደድ ብቻ ሳይሆን ምክራቸውን ተግባራዊ ታደርጋላችሁ ብለን እናምናለን። ልጆችዬ፣ ምክሩ ለእናንተ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ወላጆች የሚጠቅም ነው ብለን እናስባለን።

ልጆችዬ፣ እንደምታውቁት በየሳምንቱ ለእናንተ የሚሆን፣ እናንተ ብታነቡት ትጠቀሙበታላችሁ ብለን ያመናቸውን ነገሮች ወደ እናንተ እናቀርባለን። እናንተም ይህን በመረዳት እንደምታነቧቸው ተስፋ እናደርጋለን። ልጆችዬ፣ በቀጣይ ሳምንት ለእናንተ የሚሆን ቆንጆ ነገር ይዘን ለመቅረብ ቃል በመግባት በዚሁ እንሰነባበት አይደል? ከመሰነባበታችን በፊት ግን የምንላችሁ አለን። ትምህርታችሁን በርትታችሁ አጥኑ። ከትምህርት ቤት ላለማርፈድ በሰዓታችሁ ተነሱ። ለትምህርት የሚሆኗችሁን እንደ ደብተር፣ እርሳስ፣ ቦርሳ፣ ላጲስ እና የመሳሰሉትን የትምህርት ቁሳቁሶች አስቀድማችሁ አዘጋጁ። በእቅድ ተመሩ። በትምህርት ቤት ቆይታችሁ ደግሞ አትረብሹ። ትኩረታችሁንም ትምህርት ላይ ብቻ አድርጉ፣ እሺ ልጆች። በሉ ልጆችዬ፣ መልካም ሳምንት ይሁንላችሁ።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ